አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

### የመምህር መምሪያ



## ፯ ኛ ክፍል

አማርኛ

እንደመጀመሪያ ቋንቋ

የመምህር መምሪያ

፯ (7ኛ) ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

አዘጋጆች፡-

ማርዬ ጌትነት ስንቴ

ብርሃኑ ካሳ ረታ

አለማየሁ ደስታው ዳመና

ገምጋሚና አርታኢዎች፡-

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ሀይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

ጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ፡-

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

አቀማመጥ እና ስዕል፡-

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (TMS)

© መብቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተጠበቀ ነው።
2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል።

ለሥራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል።

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ማውጫ ገፅ

መግቢያ ------------------------------------------------------------

ምዕራፍ አንድ፡- ተፈጥሮን ማድነቅ----------------------------------1

ምዕራፍ ሁለት፡- የቤተሰብ እቅድ-----------------------------------15

ምዕራፍ ሶስት፡- በጎ ፍቃደኝነት--------------------------------------27

ምዕራፍ አራት፡- የታዋቂ ሰዎች የህይወት ታሪክ-----------------39

ምዕራፍ አምስት፡- ውሃና ጥቅሙ-----------------------------------54

ምዕራፍ ስድስት፡- የሰዎች ዝውውር--------------------------------69

ምዕራፍ ሰባት፡- ማህበራዊ ግንኙነት--------------------------------82

ምዕራፍ ስምንት፡- ሱስ---------------------------------------------94

ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የሀገር ፍቅር-------------------------------------110

ምዕራፍ አስር፡- ቃላዊ ግጥም------------------------------------123

ዋቢ ጽሑፎች

አባሪዎች

# መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው የ7ኛ ክፍል የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ አማርኛን በመጀመሪያ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ፤ በተጨማሪም የቃላትና የሰዋስው እውቀት እንዲያዳብሩ ለማድረግ የተዘጋጀ የሥርዓተ ትምህርት አካል ነው። የመምህር መምሪያው በሥርዓተ-ትምህርቱ ላይ በመመስረት በአዳዲሶቹ የመማሪያ-ማስተማሪያ መሣሪያዎች ውስጥ በጥቅም ላይ ስለዋሉት የማስተማር አቀራረቦችና ስለአዲሱ መርሃትምህርት (ሥርዓተትምህርት) መነሻ ሀሳቦች አስፈላጊ መረጃ ይሰጣል። በአንድ ምዕራፍ ሥርም ለቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ግልጽ መመሪያ ያቀርባል። በተጨማሪም ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ለመከታተልና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ተገቢውን ድጋፍና ማጠናከሪያ ለመስጠት ተከታታይ ምዘናን መተግበር የሚቻልበትን መርሕ ይዟል። በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሥርዓተፆታንና የአካቶትምህርትን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚገባ ድጋፍ ይሰጣል።

በመጨረሻ ላይም ለ7ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ) መርሃት-ምህርት ተያይዟል። ይህ መርሃ ትምህርትም በየደረጃው በእያንዳንዱ ወሰነ ትምህርት ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው ስለሚገቡ የቋንቋ ብቃቶች ያሳያል።

# የማስተማር መርሆዎች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በሁሉም ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) እንዲሁም ቃላትና ሰዋስው የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች የማንበብንና የመጻፍን ችሎታዎች በሚያዳብሩበት መልክ ተደራጅተዋል፡፡

አዳምጦ/አንብቦ መረዳት የሚዳብረው በቅድመ ማዳመጥ/ማንበብ፣ በማዳመጥ/በማንበብ ሂደትና በድኅረ ማዳመጥ/ማንበብ ተግባራት ነው፡፡ ተማሪዎች ስለጽሑፉ (በቅድመ ማዳመጥ/ማንበብና በማዳመጥ/በማንበብ ሂደት ወቅት) እንዴት መገመት እንደሚችሉ፣ መረዳታቸውን በራሳቸው እንዴት መከታተል እንደሚችሉና ያዳመጡትን ወይም ያነበቡትን እንዴት መገምገም እንደሚችሉ መማር አለባቸው፡፡

መናገርና መጻፍ በተገቢ ሁኔታ የራስን ሀሳብ መግለጽን ይመለከታል፡፡ ይኸውም ቋንቋውን በትክክል መጠቀምንና ሀሳብን ለሌላ አካል በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልጽ ማስተላለፍን ይጨምራል፡፡ በመሆኑም የንግግርና የጽሑፍ ክሂል የሚዳብረው ተማሪዎች በተቻለ መጠን ራሳቸውን እንዲገልጹ በርካታ ልምምዶች ሲመቻቹላቸውና ወቅታዊ ግብረመልሶችም ሲያገኙ ነው፡፡

የቃላት ዕውቀት፣ ቃላትን የመለየት/የመረዳትና ፍቻቸውን የመገንዘብ ችሎታ ነው፡፡ የቃላት ዕውቀት ውስንነት ያላባቸው ተማሪዎች የሚያነቡትንም ሆነ የሚያዳምጡትን ጽሁፍ መልእክት ለመረዳት ስለሚቸገሩ የቃላት እውቀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የቃላት ዕውቀት የሚዳብረው አዳዲስ ቃላትን ከነፍቻቸው በማስተማር፣ ተማሪዎች እነዚህን ቃላት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ እንዲጠቀሙባቸው በማበረታታትና ከሚያነቡት ወይም ከሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ የቃላትን ፍቺ የሚያገኙበትን ብልሃት በማስተማር ነው፡፡

ሰዋስው፡- በመርሃ ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ ለደረጃው በተዘጋጀው የትምህርት ወሰንና ተለጣጥቆ መሠረት የተለያዩ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በመማርና በትክክል በመጠቀም ላይ ያተኩራል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የዘረዘርናቸው የትምህርት ይዘቶች ማዕከል ያደረጉት በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ዓላማዎች ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ (፩)

## ተፈጥሮን ማድነቅ

(ክፍለ ጊዜ 9)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- የሌሎችን ሀሳብ ያዳምጣሉ፡፡
- ስለተፈጥሮ ምንነት ይወያያሉ፡፡
- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ፅሁፍ ያነባሉ፡፡
- የተፈጥሮን የተለያየ ገጽታ ያደንቃሉ፡፡
- አንቀፅ ይመሰርታሉ፡፡

**የትምህርት ይዘቶች**

- የሌሎችን ሀሳብ መስማት
- ተገቢ የቋንቋ አጠቃቀም
- የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላት
- አንቀፅ መፃፍ
- ተዘውታሪ ቃላት
- የቋንቋ መሰረታዊ መዋቅር

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

የትምህርቱ አቀራረብ

ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር

- ✓ በቅድሚያ ለተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉና ግልፅ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው፡፡
- ✓ "ያመቻል" በሚሉት መንገድ ተማሪዎች ቡድን እንዲመሰርቱ አድርገው በቅድመ ማዳመጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ከየቡድኖቹ በውይይት የደረሱበትን መደምደሚያ በመቀበል ያለውን የእውቀት ክፍተት ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ የምንባቡን ቅጅ ይስጧቸው፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው።

✓ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ፤ ከዚያም የቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው።

✓ ተማሪዎቹ እየተከታተሉ መሆናቸውንም ያረጋግጡ።

አዳምጦ መረዳት

ተግባር አንድ

✓ የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፤ በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ።

ተግባር ሁለት

✓ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ። በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ።

# “አባይ”

አባይ ከዓለማችን ረጃጅም ወንዞች መካከል በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡ 6696 ኪ. ሜትር እንደሚረዝም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ወንዙ 2700 ሜትር ኪዩብ በሰከንድ ይፈሳል፡፡ አማዞን ወንዝን እንደ ምሳሌ ብናነሳ ከአባይ ወንዝ አንጻር 65 እጥፍ ያህል ይፈጥናል፡፡ አባይ 70 በመቶ የሀገሪቱን ወንዞች የውሃ ድርሻ ሲይዝ አጠቃላይ የውሃ ድርሻም ቢሆን 50 በመቶ የሚጠጋ ነው፡፡ ስለዚህ አባይ ለግብፅ እና ለሱዳን ዋና የውሃ ምንጭ እንደሆነው ሁሉ ለኢትዮጵያም ወሳኝ ወንዟ ነው፡፡

የአባይ ተፋሰስ ሀገራት የሚባሉት አስር ሲሆኑ፣ እነሱም፡- ኢትዮጵያ፣ ብሩንዲ፣ ታንዛኒያ፣ ሩዋንዳ፣ ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ሱዳን፣ ግብፅ እና ደቡብ ሱዳን ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ላይ የመሰረት ድንጋዩን በመጣል የታላቁን ሕዳሴ ግድብ በመገንባት ላይ ትገኛለች፡፡ ግድቡ በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በጉባ ወረዳ ይገኛል፡፡ ግድቡን ለመገንባት የሚያስፈልገው ገንዘብ 80 ቢሊዮን ብር እንደሆነ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ፅህፈት ቤት መረጃ ያሳያል፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከተነበበው ስለአባይ ወንዝ ምን አዲስ እውቀት አገኛችሁ? በቀጣዩስ ክፍል ምን አዲስ እውቀት የምታገኙ ይመስላችኋል?

የዋናው ግድብ ከፍታ 145 ሜትር ሲሆን፣ እርዝመቱ 1.8 ኪ.ሜትር ነው፡፡ የዋናው ግድብ ውፍረት የግድቡ ግርጌ ላይ 130 ሜትር ሲሆን፣ የግድቡ ጫፍ ወይም የላይኛው ክፍል 11 ሜትር ነው፡፡ ግድቡ የሚይዘው የውሃ መጠን 74 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ሲሆን፣ ግድቡ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ደግሞ 1680 ስኩየር ኪ.ሜትር

ነው፡፡ የግድቡ ሀይል ማመንጫ ዩኒቶች 16 ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ዩኒት የሚያመነጨው የሀይል መጠን ከ375 እስከ 400 ሜጋ ዋት ነው፡፡ በአጠቃላይ የህዳሴው ግድብ 6450 ሜጋ ዋት ሀይል ማመንጨት ይችላል፡፡

ከግድቡ የሚገኘው ሀይል ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ከመዋል ባለፈ የሚተርፈውንም ማለትም 2000 ሜጋ ዋት ያህሉን ለጎረቤት ሀገራት በመሸጥ በዓመት እስከ 580 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት ይቻላል ተብሎ ተተንብይዋል፡፡ ባለፈው ዓመት የመጀመሪያው ዙር የግድቡ ሙሌት የተከናወነ ሲሆን በዚህም 4.9 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ የመያዝ ውጥን ተሳክቷል፡፡ በዚህ ዓመትም ተጨማሪ 13.5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ውሃ ለመያዝ ታቅዶ በስኬት ተጠናቋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የግድቡ ግንባታ 80 በመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ግድቡ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ሀይል የማመንጨት ስራው ሲከናወን የሀገራችንን ልማት የሚያፋጥን ይሆናል፡፡

ምንጭ፡- (ዝክረ ህዳሴ አዲስ አበባ፣2013 ዓ.ም ከገፅ 58-59)

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ተፈጥሮን በተመለከተ ጥያቄ በመጠየቅ ምን ያህል እንደተገነዘቡ ያረጋግጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (እንደ አስፈላጊነቱ)

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

“የአባይ ወንዝ እና የህዳሴው ግድብ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. መ
2. ሐ
3. ለ
4. ሀ
5. ለ

ተግባር ሁለት፡-

ካዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. አበርክቶ
2. አጠቃቀም
3. እቅድ
4. ተገምቷል
5. የውሃ ማለፊያ
6. ቁመት
7. በመጀመሪያ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ማስታወሻ:- የንግግር መመሪያ

ንግግር በቃል ወይም በጽሁፍ ሊቀርብ የሚችልና ሀሳብ አፍልቀን ለሌሎች የምናስተላልፍበት ክሂል ሲሆን ከዝግጅት እስከ አቀራረብ ጥንቃቄን የሚፈልግ ነው፡፡

ሀ. የንግግር አዘገጃጀት፡- ንግግር ለማድረግ ስንነሳ የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን፡፡

- የአድማጭን እድሜ፣ ፆታና የእውቀት ደረጃ ማወቅ
- የርዕሱን ጥልቀት መወሰን
- መረጃ መሰብሰብ
- ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለንግግሩ የሚያስፈልጉትን መለየት
- ንግግሩን በቅደም ተከተል ማደራጀት
- ፍሬ ሀሳቦችን በአሃዝ ከፋፍሎ ለማየት በሚያስችል መልኩ ማደራጀት

ለ. የንግግር አቀራረብ

- ርዕሱን ማስተዋወቅ
- የንግግሩን ዓላማ ባጭሩ መግለፅ
- የድምጽ ቃና፣ አወራረድና ፍጥነትን መወሰን
- የአካል እንቅስቃሴው አድማጭን የሚማርክ እንዲሆን መጣር
- የተደራሲያንን ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ
- ተደራሲያንን በዓይን መቃኘት
- ለቃላት ምርጫ ልዩ ትኩረት መስጠት
- በመጨረሻ ከአድማጭ አስተያየት መቀበል የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ተግባር አንድ

- ✓ ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎቹ ግልፅ በሆነ መንገድ ያብራሩላቸው፡፡
- ✓ የማዳመጥ ምንባቡን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ትዕዛዝ በመከተል ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የቡድን ውይይቱን ከጨረሱ በኋላ ከቡድኑ አንድ ሰው በመምረጥ ንግግር ያቀርቡ ዘንድ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ወደ ተግባር ሁለት በመሻገር ትዛዙን መሰረት በማድረግ እርስ በርስ ግብረ መልስ እንዲሰጣጡ ያግዟቸው፡፡

ምዘና፡-

- የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላትን መለየት መቻላቸውን በጥያቄ ያረጋግጡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ

ቅድመ ንባብ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ወደ ንባብ ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጥያቄዎችን ያንበቡላቸው

የንባብ ጊዜ

ተግባር

- ✓ ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ያሉትን አንቀፆች በግላቸው እንዲያነቡ ተማሪዎችን ይዘዟቸው፡፡
- ✓ አንቀፆቹ ከተነበቡ በኋላ የንባብ ጊዜ ጥያቄን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲቀጥሉ ይዘዟቸው፤ ይከታተሏቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ምንባቡ እንዲነበብላቸው ያድርጉ፤ ድጋፍም ይስጧቸው፡፡

አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ተማሪዎቹ ንባባቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመሄድ ተግባር አንድ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡

ተግባር ሶስት

- ✓ በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት መምህሩ መመሪያ ላይ ማስታወሻውን ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም ተራ በተራ በማስነሳት ድምፃቸው ከፍ አድርገው ምንባቡን በትክክል እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

## ማስታወሻ

### ጥሩ የንባብ ልምዶችን ማዳበር

ሰዎች ሃምሳ በመቶ ያህሉን እውቀት የሚገበዩት ከንባብ መሆኑ ይገመታል፡፡ ይህ ግምት ትክክለኛ ከሆነ ንባብ እውቀትን ለመቅሰሚያ አይነተኛ መሳሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የተፃፈ ነገር ሲነበብ አንባቢው ቃላት የተደረደሩበትን መስመር ከግራ ወደ ቀኝ በዓይኖቹ ይቃኛል፡፡ ይህ የማንበብ ተግባር የሚከናወነው ዓይኖች በቃላት ላይ በሚያርፍበት ቅፅበት ነው፡፡ በሌላ በኩል የንባብ ፍጥነት ከአንባቢ አንባቢ ይለያያል፡፡ ስለሆነም በደቂቃ በርካታ ቃላትን የማንበብ ችሎታ ያለው ሰው የንባብ ፍጥነት የሌለውን ሰው ጊዜ በመቆጠብ ይበልጠዋል፡፡ በሚቆጥበው ጊዜም ጠቃሚ ተግባሮችን ማከናወን ይችላል፡፡

ጥሩ አንባቢ የሚያነበውን ለመረዳትና ለማስተዋል ጥረት ያደርጋል፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች የሚያነቡትን ነገር ለማስተዋል ከሚረዱት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

1. የጽሁፉን ሀሳብ በጥልቀት ማየትና መገምገም፣
2. የበለጸገ የቃላት እውቀት፣
3. ሁለገብ የሆነ የሕይወት ልምድና ጠቅላላ እውቀት መገብየት፣

አንድን ጽሁፍ አንብቦ ፍሬ ነገሮችን ለመጨበጥ ደግሞ፡-

1. በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ብዙ ገፆችን በማንበብ መለማመድ፣
2. በንባብ ወቅት በዋና ዋና ሀሳቦች ላይ ትኩረት ማድረግ፣
3. ዓረፍተ ነገሮችን በሀረጎቻቸውና በሃሳብ ቅደም ተከተላቸው ከፋፍሎ ለማንበብ መሞከር፣
4. አዳዲስ ቃላትና ሀረጎችን ማጥናት፣
5. ንባብን ለማሻሻል የሚወጡ መመሪያ አዘል መጻህፍትን በማንበብ የንባብ ችሎታና ልምድን ማዳበር የሚሉት ናቸው፡፡

ምዘና፡-

- በትዕዛዙ መሰረት አንቀጽ መጻፋቸውን ያረጋግጡ
- በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ሀይለ ቃሉን ለይተው እንዲያወጡ ያድርጉ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት፡-

በ “ሀ” ስር ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ቃላት በ “ለ” ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ረ | 4. ለ |
| 2. ሀ | 5. ሠ |
| 3. ሰ | 6. ሐ |

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ አንቀፅ የሚለውን ማስታወሻ ተማሪዎች በተናጥል እንዲያነቡ እና በጥንድ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡
- ✓ ቱሪዝም በሚል ርዕስ በቀረበው ቢጋር መሰረት ተማሪዎች ሁለት አንቀፅ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ተማሪዎች በፃፉት አንቀፅ ዙሪያ ደብተራቸውን ተቀያይረው የእርስ በርስ ግምገማ እንዲያደርጉ ድጋፍ እና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም በቀረቡት አንቀፆች ላይ አጠቃላይ ግበረ -መልስ ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- አንቀፁን በትክክል መፃፍ እና አለመፃፋቸውን ያረጋግጡ

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ የቀረበውን ማስታወሻ በተናጥል እንዲያነቡ ያድርጉ
- ✓ ተማሪዎቹ መረዳታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የገቡትን ተዘውታሪ ያልሆኑትን ቃላትን በማውጣት እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ዐረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

ምዘና፡-

- ተዘውታሪ እና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን መለየታቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- ተዘውታሪ እና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ያዘጋጁ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን በመለየት ፃፉ፡፡

1. ሙግት
2. ዋዜማ
3. ሰርክ
4. አዘቦት እና የውሃ ሽታ
5. አጎናት
6. ጥቁር እንግዳ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ባለው ማስታወሻ መሰረት ለተማሪዎች ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ በማለት እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት፡-

✓ ተማሪዎቹ በራሳቸው ነጠላ እና ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

| ማስታወሻ |
|---|
| **ዓረፍተ ነገር** |
| ዓረፍተ ነገሮች ከመዋቅር (ከቅርፅ) አንጻር ነጠላ እና ውስብስብ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡- |
| ሀ. ነጠላ ዓረፍተ ነገር፡- ነጠላ ዓለፍተ ነገር የሚባለው በውስጡ አንድ ግስ ብቻ የያዘ የዓረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡ |
| ምሳሌ፡- ለምለም ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡ |
| ለ. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር፡ ወስብስብ ዓረፍተ ነገር የሚባለው በውስጡ ሁለት እና ከዚያ በላይ ግሶችን የያዘ የዓረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡ |
| ምሳሌ፡- አሉላ አባቱ ስለመጣ ደስ አለው፡፡ |

ምዘና፡-

- ስለ ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ልዩነት ይጠይቋቸው

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

መምህራችሁ በሰጧችሁ ማስታወሻ መሰረት ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ በማለት ለዩ፡፡

1. ነጠላ
2. ውስብስብ
3. ነጠላ
4. ውስብስብ
5. ነጠላ

# ምዕራፍ ሁለት (፪)

## የቤተሰብ እቅድ

(ክፍለ ጊዜ 9)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- ➢ በጥሞና ያዳምጣሉ፡፡
- ➢ በቤተሰብ እቅድ ምንነት ላይ ይወያያሉ፡፡
- ➢ ቀላል ሁነቶችን ይተርካሉ፡፡
- ➢ የቤተሰብ እቅድን መሰረት አድርገው በሚሰጡ አስተያየቶች ላይ ይከራከራሉ፡፡
- ➢ ስዕሎችን ያብራራሉ፡፡

**የትምህርት ይዘቶች**

- በአትኩሮት ማዳመጥ
- ሁነቶችን መተረክ
- አንብቦ መግለፅ
- ኢ-መደበኛ ጽሁፍ
- የአዳዲስ ቃላት ፍቺ
- የአሁን ጊዜ

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር

- ✓ ለተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉና ግልጽ ያልሆኑ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው፡፡
- ✓ "ያመቻል" በሚሉት መንገድ ተማሪዎች ቡድን እንዲመሰርቱ አድርገው በቅድመ ማዳመጥ በቀረቡት ሶስት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፤ ምላሻቸውንም ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ከየቡድኖቹ በውይይት የደረሱበትን መደምደሚያ በመቀበል ያለውን የእውቀት ክፍተት ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡
- ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ የምንባቡን ቅጅ ይሰጧቸው፡፡

### የማዳመጥ ጊዜ

### ተግባር አንድ

- ✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ፡፡ ከዚያም የቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ የመስማት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ የምንባቡን ቅጂ እንዲያነቡ ያድርጉ፤ እገዛም ይስጧቸው፡፡

- ✓ ማዳመጡ እንዳለቀ ለቀረቡት ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ቁልፍ ቃላት እና ሀረጋት በቀረቡት ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው እንዲያስገቡ ያድርጓቸው፡፡

“ልጅ በእድሉ ያድጋል”

የጥሩ ጓደኝነት ተምሳሌት መሆናቸውን ሁሉም ሰው ሽንጡን ገትሮ ይከራከርላቸዋል፡፡ ህብስት እና ዘምዘም ከልጅነታቸው ጀምሮ አብረው ጭቃ አቡክተው፣ አፈር ፈጭተው ያደጉ ባልንጀሮች ናቸው፡፡ ሁለቱም ከአፀደ ህፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ የተማሩት አብረው ነው፡፡ በትምህርታቸውም ታታሪና ጠንካራ ተማሪዎች ነበሩ፡፡

ህብስት ወደ ስራው ዓለም የተቀላቀለችው ወዲያው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንደጨረሰች ነበር፡፡ ለአንድ ዓመት ያህል እንደሰራች በአጋጣሚ ከተዋወቀችው ከተፈራ ፍርድ አወቅ ጋር ሶስት ጉልቻ መስርተው አብረው መኖር ጀመሩ፡፡ የትዳር አጋሯ ልጅ በእድሉ ያድጋል የሚል የተዛባ አመለካከት በመያዙ የስነ-ተዋልዶ አገልግሎት ባለመጠቀማቸው በአስራ ሁለት ዓመት ውስጥ በአናት በአናቱ አራት ሴት እና ሁለት ወንድ ልጆችን ወለዱ፡፡ ነገር ግን የባል እና የሚስት የወር ገቢ ልጆችን ለማስተማር ይቅርና የእለት ጉሮሯቸውን ለመድፈን እንኳን የማይችሉበት ደረጃ ደረሱ፡፡ በዚህም ምክንያት ቤተሰቡ ሰላም አጣ፡፡ ነጋ ጠባ ፀብ እና ጭቅጭቅ የዚህ ቤተሰብ መገለጫ ሆነ፡፡ ተፈራም ዶሮ ሳይጮህ ከቤት እንደወጣ እኩለ ሌሊት ላይ ጥንብዝ

ብሎ ሰክሮ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ በስካር መንፈስም ቤተሰቡን እና ጎረቤቶቹን ሰላም ሲነሳ ያድራል፡፡

የሁለቱም ቤተሰቦች እና ጎረቤቶች በቤቱ ውስጥ ሰላም ለማውረድ በተደጋጋሚ ቢያሸማግሏቸውም ሰላም ሊወርድ አልቻለም፡፡ ይባስ ብሎ ተፈራ ህብስትን ምክንያት እየፈለገ ይደበድባት ጀመር፡፡ ልጆቹም የሚላስ የሚቀመስ ከቤት ሲጠፋ፣ ትምህርታቸውን አቋርጠው ጎዳና ለመውጣት ተገደዱ፡፡ በመጨረሻም በእቅድ ያልተመራው የሕብስት እና የተፈራ ትዳር በአሳዛኝ ሁኔታ ፈረሰ፡፡

* እስካሁን ካዳመጣችሁት የነህብስት ታሪክ ምን ቁም ነገር አገኛችሁ? ስለ ዘምዘም ታሪክስ ምን ትገምታላችሁ?

ዘምዘም ግን የከፍተኛ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች ወዲያውኑ ወደ ስራ ዓለም በመግባት የራሷን እና የወላጆቿን ህይወት ለማሻሻል ደፋ ቀና ማለት ጀመረች፡፡ ከአምስት ዓመት በኋላ ከምትወደው እና ባህሪውን በቅርበት ከምታውቀው የስራ ባልደረባዋ የሱፍ አህመድ ጋር በትዳር ተጣመሩ፡፡ ከባለቤቷ ጋር በመመካከር በአካባቢያቸው ወደሚገኝ የጤና ተቋም በመሄድ፣ የስነ-ተዋልዶ አገልግሎት በመውሰድ እና በእቅድ በመመራት የበኩር ልጇን ኑረዲንን ተገላገለች፡፡ ከሶስት ዓመት በኋላም ሴት ልጅ በሰላም ተገላገለች፡፡

ነገር ግን ኑረዲን የጤና ችግር አጋጠመው፡፡ ይህ ችግር ኑረዲንን እንደፈለገ በእግሩ እንዳይሄድ ቢያደርገውም ቤተሰቦቹ ተስፋ ሳይቆርጡ፣ ተገቢውን ድጋፍ እና እንክብካቤ ያደርጉለት እና ትምህርቱን ያስተምሩት ጀመር፡፡ ምክንያቱም በቤተሰብ እቅድ በመጠቀማቸው ችግሩን በመቋቋም ሁለቱ ጥንዶች ልጆቻቸውን በጥሩ ትምህርት ቤት እያስተማሩ፣ በፍቅር እና በእንክብካቤ በማሳደግ ለቁም ነገር አበቁ፡፡

የህብስትን እና የዘምዘምን የህይወት መንገድ መለያየት ያስተዋሉ የድሮ የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው "ልጅ በእድሉ ያድጋል" ፡፡ የሚለውን ብሂል መነጋገሪያ አድርገውታል፡፡

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- ስለ ቤተሰብ ምጣኔ ጠቀሜታ ጥያቄ ይጠይቋቸው

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (እንደ አስፈላጊነቱ)
- ስለ ቤተሰብ ምጣኔ የሚያሳዩ ስዕሎች (ቻርቶች)

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት፡-

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ቁልፍ ቃላት እና ሀረጋት ከታች በቀረቡት ያልተሟሉ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢው ቦታቸው አስገቡ፡፡

1. የበኩር
2. ደፋ ቀና
3. ዶሮ ሳይጮህ
4. ባልደረባ
5. ባልንጀራ

ክፍል ሁለት፡- መናገር

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

- ✓ የቀረበውን ቢጋር መሰረት በማድረግ የሁነቶችን ቅደም ተከተል በመጠበቅ በየተራ ንግግር እንዲያደርጉ ያግዟቸው፤ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡
- ✓ የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ "ልጅ በእድሉ ያድጋል" የሚለውን ሀሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም ተማሪዎቹ በቡድን ክርክር እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡ ለክርክር የሚያግዝ ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡

ማስታወሻ

ክርክር

ክርክር ሁለት ሰዎች ወይም ሁለት ቡድኖች ዳኞችን በመሰየም የሚያደርጉት ስርዓት ያለው ሙግት ነው፡፡

1. የክርክር ዝግጅት፡- በክርክር ዝግጅት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች መመልከት ያስፈልጋል፡፡
   - ርዕሱን በሚመለከት ከተለያዩ ምንጮች መረጃ መሰብሰብ፡፡ ምሳሌ፡- ከባለሙያዎችና ከልዩ ልዩ ጽሁፎች
   - ከተገኘውና ከተነበበው መረጃ ውስጥ ለክርክር ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
   - ክርክሩ ለአድማጭ ከመቅረቡ በፊት ከጓደኛ ወይም ከቤተሰብ አባላት ፊት ልምምድ ማድረግ
   - ለክርክር ከመቅረብ በፊት ስብዕናን ማሟላት፡፡ ምሳሌ፡- ንጽህናና አለባበስን ማስተካከል

2. የክርክር አቀራረብ፡- በክርክር አቀራረብ ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

- የመከራከሪያ ርዕስን ለአድማጭ ማስተዋወቅ
- ፍሬ ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ማቅረብ
- ረጋ ባለ መንፈስ በልበ ሙሉነት ማቅረብ
- ክርክሩ በሚቀርብበት ጊዜ ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ አለማድረግ
- ከተቃራኒ ቡድን የሚሰጡ ሀሳብን በትክክል ማዳመጥ፣ ማስታወሻ መያዝና የተቃውሞ ሀሳብ ማዘጋጀት
- ሀሳብ እያነበቡ አለማቅረብ
- የአድማጭን ችሎታ አቅምን ያገናዘበ ሀሳብን ማቅረብ
- ለክርክሩ የተሰጠውን ጊዜ ማክበር
- ከርዕሱ ውጭ የሆነ ሀሳብ አለማቅረብ
- አድማጭን ማመስገን የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ምዘና፡-

- የሁነቶችን ቅደም ተከተል ጠብቀው ንግግር ማድረጋቸውን ያረጋግጡ
- ክርክሩን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይገምግሙ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የሁነቶችን ቅደም ተከተል የሚያሳይ የቢጋር ሰንጠረዥ

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ንባብ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ወደ ማንበብ ሂደት ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ የተማሪዎችንም ምላሽ ይቀበሏቸው፡፡

### የንባብ ጊዜ

ተግባር

- ✓ ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ያሉትን አንቀፆች በለሆሳስ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፤
- ✓ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል በየግላቸው እንዲያነቡ ይዘዟቸው፤ ይከታተሏቸው፡፡
- ✓ አይነ ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ ምንባቡ እሰዲነበብላቸው ያድርጉ፡፡

አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ተማሪዎቹ ንባባቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመሄድ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡

ተግባር ሶስት

- ✓ በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ምንባቡን እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር አራት

- ✓ የቀረበውን ምስል በመመልከት ተማሪዎቹ የተረዱትን መልእክት በሁለት አንቀፅ እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ስለ ስዕሉ ገለፃ ያርጉላቸው፡፡

ምዘና፡-

- ምንባቡን በተገቢው መንገድ ማንበባቸውን ይከታተሉ
- የቀረበውን ምስል መሰረት አድርገው ሁለት አንቀፅ መጻፋቸውን ይመልከቱ፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ቃላት በምንባቡ አውድ መሰረት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

1. ሰ
2. ሀ
3. ሐ
4. ሸ
5. ለ
6. መ
7. ረ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ ስለ መደበኛ እና ኢ መደበኛ ፅሁፍ የቀረበውን ማስታወሻ ተማሪዎች በተናጥል እንዲያነቡ እና በጥንድ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ባለ ሶስት አንቀፅ ኢመደበኛ ፅሁፍ እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ በተግባር አንድ የቀረበውን ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ የጻፉትን ባለ ሶስት አንቀፅ ኢ-መደበኛ ፅሁፍ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተራረሙ ያድርጉ፤ በድጋፍ እና ክትትልም ያግዟቸው፡፡

ምዘና፡-

- ባለ ሶስት አንቀፅ ኢ-መደበኛ ጽሁፍ መፃፋቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የኢ-መደበኛ ፅሁፍ ሞዴል አንቀፅ

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

- ✓ ከቀረበው አንቀፅ ውስጥ ለወጡ አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ምዘና፡-

- ለቀረቡት አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡-

- የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

### በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ቀጥሎ የቀረበውን አንቀጽ በማንበብ ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ውጤታማነት
2. የሌለው
3. ቆይቶ
4. የተሻለ ቦታ
5. አጋጣሚ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ በቀረበው ማስታወሻ መሰረት ተማሪዎች እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች የአሁን ጊዜ መሆንናቸውና አለመሆናቸውን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ አምስት የአሁን ጊዜን የሚያመለክቱ ዐረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

ምዘና፡-

- የአሁን ጊዜን የሚያሳይ ዐረፍተ ነገር መመስረታቸውን ይመልከቱ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች የአሁን ጊዜ ከሆኑ አዎ ካልሆኑ አይደለም በማለት መልሱ፡፡

1. አይደለም
2. አይደለም
3. አዎ
4. አይደለም
5. አይደለም
6. አዎ

# ምዕራፍ ሶስት (፫)

## በጎ ፍቃደኝነት

(ክፍለ ጊዜ 9)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- ያዳመጡትን ያነፃፀርቃሉ።
- ስለበጎ ፍቃደኝነት ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ።
- የፅሁፉን ዋና ሀሳብ መልሰው ይገልፃሉ።
- በጎ ፍቃደኞች በምን በምን ዙሪያ እንደተሰማሩ ይለያሉ።
- ከፅሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ያወጣሉ።

### የትምህርት ይዘቶች

- ማዳመጥ እና ማነፀባረቅ
- ከጓደኛ ጋር ምልልስ ማድረግ
- አዳምጦ ዋናውን መልዕክት መናገር
- አሳማኝ ፅሁፍ
- ድርብ ቃላት
- ነጠላና ብዙ ቁጥር

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## ማስታወሻ

### የማዳመጥ መመሪያ

ማዳመጥ የሚከናወነው በንቃት በመሆኑ ንቃትን ከማይጠይቀው ከመስማት እጅግ ይለያል፡፡ በማዳመጥ ሂደት ውስጥ ሁልጊዜም መረዳትና ማገናዘብ ይኖራል፡፡

የጥሩ አድማጭ መገለጫ ባህሪያት፡ ማዳመጥ የሰው ልጅ ተግባቦታዊ ሂደት መሰረት ነው፡፡ ከመናገር፣ ከመጻፍና ከማንበብ በበለጠ ብዙ ጊዜ የምናጠፋው በማዳመጥ ነው፡፡ የማዳመጥን ችሎታ ለማሳደግና ለማዳበርም ከዚህ ቀጥለው በቀረቡት ነገሮች ላይ መመስረት አስፈላጊ ነው፡፡

1. ንቁ ተሳታፊ መሆን፡- በማዳመጥ ወቅት ሁሉ መሳተፍ አስፈላጊ ነው፡፡ አስተያየት መስጠት ወይም ጥያቄ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡
2. ማስታወሻ መያዝ፡- ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ላይ መዝግቦ መያዝ የማዳመጥን ችሎታ ያሣድጋል፡፡
3. ትኩረት ማድረግ፡- ትኩረታችንን ሙሉ በሙሉ በሚደመጠው ነገር ላይ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡
4. ከስሜታዊነት ነፃ መሆን፡- ስሜታዊ የሆነ ሰው የማያምንበት ወይም የማይመስለው ነገር በተነገረ ቁጥር ብስጭትን ትቶ ራስን ተቆጣጥሮ መከታተል አስፈላጊ ነው፡፡
5. ትኩረትን የሚበትኑ ነገሮችን ማስወገድ፡- ለማዳመጥ ስንጀምር ትኩረታችንን ሊበትኑ የሚችሉ ነገሮችን ለማስወገድ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡
6. ትክክለኛ የመቀመጫ ቦታ መምረጥ፡ ፀጥታ ያለበት እና ምቹ ቦታ መምረጥ

7. የሌሎችን ሀሳብ ማክበር፡- እያንዳንዱ ሰው የራሱ እምነትና አመለካከት ስላለው የሰዎችን አመለካከት ማክበር ይኖርብናል። በሀሳቡ ላይ ልዩነት ካለን ደግሞ በአግባቡ ጥያቄ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር

- ✓ በቅድሚያ ለተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው፡፡
- ✓ ከላይ የቀረበውን የማዳመጥ መመሪያ ለተማሪዎቹ በሚመች መልኩ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ያመቻል በሚሉት መንገድ ተማሪዎች ቡድን እንዲመሰርቱ አድርገው በቅድመ ማዳመጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ከየቡድኖቹ በውይይት የደረሱበትን መደምደሚያ በመቀበል ያለውን የእውቀት ክፍተት ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ የመስማት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ የምንባቡን ቅጂ እንዲያነቡ ያድርጉ፤ እገዛም ይስጧቸው፡፡

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ፡፡ ከዚያም የቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር አንድ

✓ "የበጎ ፍቃደኝነት ተምሳሌት" በሚል ርዕስ ባዳመጡት ምንባብ መሰረት የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

### ተግባር ሁለት

✓ የቀረበውን የአዛምድ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ በሚሰሩበት ጊዜም ማስተካከያ ይስጡ፡፡

## "የበጎ ፍቃደኝነት ተምሳሌት"

የተወለዱት ጥር 9 ቀን 1951 ዓ.ም በአዲስ አበባ ነው፡፡ አባታቸው ትጉህ ሰራተኛ ነበሩ፡፡ ልጅነታቸውን በእረኝነት ያሳለፉት አባታቸው እውቅ የወንዶች ሙሉ ልብስ ሰፊ ነበሩ፡፡ ገጠር የተወለዱት እናቷ የዘጠኝ ዓመት አፍላ ልጅ እያሉ ነበር የተዳሩት፡፡ እናት አባታቸው የትምህርት ቤቱን ደጃፍ አልረገጡም፡፡ ነገር ግን እጅግ አስተዋዮች ነበሩ፡፡

ዘሚ የኑስ በ1969 ዓ.ም ወደ ጣሊያን ሀገር ተጓዙ፡፡ ጣሊያን ውስጥ ትምህርት እየተማሩ ጎን ለጎንም በጣሊያን ማዕከላዊ የስደተኞች

ሰፈር ውስጥ ተቀጥረው መስራት ጀመሩ። በመቀጠልም በ1973 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ጥቂት ከቆዩ በኋላ ወደ አሜሪካን ሀገር ተጓዙ። እዛው እያሉ በመዋቢያ ንጥረ-ነገሮች እና አጠቃቀማቸው ዙሪያ ስልጠና ከወሰዱ በኋላ በፊልም ማዕከልነቷ በምትታወቀው ሆሊውድ እና በቤቨርሊ ሂልስ በቆዳ እና ፀጉር እንክብካቤ ላይ በማተኮር በሞያቸው ይሰሩ ጀመር።

በራሳቸው በገቡት ቃል ኪዳን መሰረት በ1983 ዓ.ም ለእረፍት ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። በስራ አጥነት ተስፋ የቆረጡ ብዙ ወጣቶችን ሲመለከቱ ልባቸው በሀዘን ተሰበረ። በዚህም ሁኔታ ወደ ሀገራቸው ጠቅልለው በመምጣት ወጣቶች እና ህፃናት ላይ በማተኮር ለሚወዷት ሀገራቸው የድርሻቸውን ለመወጣት ወሰኑ። የስራ እድል ለመፍጠር እና የሙያ ክህሎታቸውን ለወገናቸው ለማካፈል በማሰብ ፍቃድ የተሰጠውን የመጀመሪያውን የውበት ትምህርት ቤት አቋቋሙ። በዚህም ተቋም ከስድስት ሺህ በላይ ወጣት ሴቶች እና ወንዶችን አሰልጥነው አስመረቁ። በዚህ መሀል ግን የሕይወታቸውን አቅጣጫ የሚቀይር አጋጣሚ ተከሰተ። ትንሹ ልጃቸው የኦቲዝም ችግር እንዳለበት በባለሙያ ተነግሯቸው ከባድ ፈተና ውስጥ ገቡ።

* እስካሁን ካዳመጣችሁት ታሪክ ምን ቁም ነገር አገኛችሁ? በቀጣዩ የታሪክ ክፍልስ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

ልጃቸውን የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ቢያስገቡም ሁሉም ትምህርት ቤቶች “የተለየ ባህሪ አለው” በማለት ከትምህርት ገበታው አሰናበቱት። ከዚህ በኋላ እርሳቸው ይህን በመገንዘብ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች ያሏቸው ወላጆች የሚጋፈጧቸውን ፈተናዎች በቅጡ ተገነዘቡ። ኦቲዝም የጤና ችግር ሳይሆን እንደ እርግማን እየተቆጠረ በርካታ ህፃናት አንዳች ነገር ተጠናውቷቸዋል እየተባሉ በሰንሰለት ታስረው ጨለማ ውስጥ እንደሚወረወሩ ያስተውሉ ነበር። አንዳንዶቹ ቤተሰቦቻቸው ሳይቀር ያገሏቸዋል።

በኢትዮጵያ በኦቲዝም የሚቸገሩ ልጆችን የማስተናገድ አቅም ያለው ትምህርት ቤት ፈልገው ሲያጡ አገራቸው ላይ ሆነው ማህበረሰቡን ስለኦቲዝም ማስተማር የሕይዎት ዓላማቸው አድርገው ተነሱ። ልጃቸውን እና ተመሳሳይ የጤና እክል ያለባቸውን ህፃናት ለመርዳት እና የእናቶችን ሸክም ለመጋራት በቁርጠኝነት ተነሱ። በ1994 ዓ.ም ጆይ የኦቲዝም ማዕከልን መሰረቱ። ማዕከሉም የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ህፃናት ተቀብሎ የሚያስተናግድ የመጀመሪያው የኦቲዝም ማዕከል ሆነ። በማዕከሉ የዚህ ችግር ያለባቸው ህፃናት በቀላሉ እንዲናገሩ እና እንዲፅፉ የሚያግዝ አቡጊዳ ፎኔቲክስ በሚል የፈጠሩት አዲስ የቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት አስገኝቶላቸዋል።

በአሁኑ ጊዜም የኦቲዝም ችግር ያለባቸው በርካታ ህፃናትን ማዕከሉ እያገለገለ ይገኛል። ወይዘሮ ዘሚ የኑስ ለልጆች ጊዜያችሁን በአግባቡ ተጠቀሙ፤ የምትሰሩትን እወቁ፤ ለሱስ ተገዢ አትሁኑ፤ ማንንም ለመምሰል ሳይሆን ራሳችሁን ለመሆን ጣሩ፤ ዓላማችሁን እውን ለማድረግ በትጋት ሰርታችሁ ስኬትን ተቀዳጁ። የሚሉ ምክሮችን ለግሰዋል። በመጨረሻም በዓለም አቀፍ እንዲሁም በሀገራችን በተከሰተው እና ብዙ ሰዎችን ለህልፈት በዳረገው የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምክንያት በ2013 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ምንም እንኳን በህይወት ቢለዩ ለሀገር እና ለትውልድ የሚጠቅም ትልቅ አሻራ አስቀምጠው አልፈዋል።

ምንጭ:- (ተምሳሌት፣ እፁብ ድንቅ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች፣ ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የቀረበ)

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- ስለ በጎ ፍቃደኝነት ምንነት ይጠይቋቸው

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (እነደአስፈላጊነቱ)

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ "ለ" ስር ከተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | መ | 5. | ሰ |
| 2. | ሐ | 6. | ለ |
| 3. | ሠ | 7. | ሀ |
| 4. | ረ | 8. | ቀ |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር


### የትምህርቱ አቀራረብ

### ተግባር

✓ ተማሪዎችን ጥንድ ጥንድ በማድረግ እርስ በርስ መረዳዳትን በተመለከተ ንግግር (ምልልስ) እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ ካቀረቡም በኋላ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

✓ እርስ በርስ መረዳዳት የሚሰጠውን ጥቅም እንዲገልፁ ያድርጉ



## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

- ✓ ተማሪዎች ወደ ማንበብ ሂደት ከመሄዳቸው በፊት የቀረበውን ሰንጠረዥ የማውቀው እና ማወቅ የምፈልገው የሚለውን ክፍል ብቻ እንዲሞሉ ያድርጓቸው፡፡

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

- ✓ ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ያሉትን አንቀፆች ተማሪዎች በለሆሳስ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ የንባብ ጊዜ ጥያቄን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል በየግላቸው እንዲያነቡ ይዘዟቸው፤ ይከታተሏቸው፡፡
- ✓ አይነ ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ ምንባቡን ያንበቡላቸው ስለ ስዕሉ ገለፃ ያደርጉላቸው፡፡

### አንብቦ መረዳት

**ተግባር አንድ**

- ✓ ተማሪዎቹ ንባባቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ ቅድመ ንባቡ ሰንጠረዥ በመመለስ ከምንባቡ ያወቅሁት የሚለውን ረድፍ እንዲሞሉ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ በመቀጠልም ወደ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመሄድ ተግባር አንድ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ለቀረቡት የተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ያግዟቸው፡፡

ምዘና፡-

- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቁልፍ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት

ከታች በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት እና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የእቅድ ዝርዝር
2. ሲተላለፍ
3. የእህል ማከማቻ
4. እያገኙ
5. ክፍያ/ድጋፍ
6. ከፍታ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ የማግባቢያ ጽሁፍ የሚለውን ማስታወሻ ተማሪዎች በተናጥል እንዲያነቡ እና በጥንድ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡ ገለፃም ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በምሳሌው መሰረት ባለ አራት አንቀፅ የማግባቢያ ፅሁፍ እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ የፃፉትን አንቀፅ መሰረት በማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር የእርስ በርስ እርማት እንዲሰጣጡ ያድርጉ፡፡

ምዘና፡-

- አግባቢ ፅሁፍ መጻፋቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የአግባቢ ፅሁፍ ሞዴል አንቀፅ

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

✓ የቀረበውን ማስታወሻ በተናጥል እንዲያነቡ በማድረግ መረዳታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ድርብ ቃላትን እንዲጽፉ ያድርጉ።

ተግባር ሁለት

✓ ካነበቡት ምንባብ አንቀፅ አንድ ላይ በመሄድ አስር ተዘውታሪ ቃላትን እንዲያወጡ ያድርጉ።

ምዘና፡-

- ድርብ ቃላትን መመስረታቸውን ያረጋግጡ
- ተዘውታሪ ቃላት ከምንባቡ ውስጥ ማውጣታቸውን ይመልከቱ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የተወሰኑ ድርብ ቃላትን ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

✓ ስለ ነጠላ እና ብዙ ቁጥር ማብራሪያ ይስጧቸው፤ በመቀጠልም በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ቃላት ነጠላ እና ብዙ ቁጥር በማለት እንዲለዩ ያግዟቸው፤ከዚያም በቃላቱ ዓረፍተ ነገር እነዲመሰርቱ ያድርጉ።

ምዘና፦

- ነጠላ እና ብዙ ቁጥሮችን መለየታቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፦

- ነጠላ እና ብዙ ቁጥሮችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

# ምዕራፍ አራት (፬)

## የታዋቂ ሰዎች የህይወት ታሪክ

(ክፍለ ጊዜ 12)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- በማዳመጥ ያብራራሉ፡፡
- የህይወት ታሪክን ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- ከፅሁፉ ውስጥ የምክንያት እና የውጤት ግንኙነትን ይለያሉ፡፡
- የታዋቂ ሰው የህይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡

**የትምህርት ይዘቶች**

- ማዳመጥ እና ማድነቅ
- መመሪያዎች
- ፈሊጣዊ አነጋገር
- አያያዥ ቃላት
- የተለመዱ ቃላት
- ሀረግ

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

የትምህርቱ አቀራረብ

ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃላቸው መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ የምንባቡን ቅጅ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ በመቀበል ያለውን የእውቀት ክፍተት ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

- ✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ፡፡ ከዚያም የቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡

አዳምጦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ማዳመጡ እንዳለቀ ወደ ተግባር አንድ በመሸጋገር ለቀረቡት የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ካደመጡት ምንባብ ለወጡ የተሰመረባቸው ቃላት ዓውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

"ዓለምፀሐይ፤ የሀገር ፀሐይ"

ስሜ አለም ጸሀይ ወዳጆ ይባላል የተወለድኩት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ እኔ በተወለድኩ ጊዜ እናቴ ገና 16 ዓመቷ ነበር፡፡ ወዲያው አባቴ በግሪክ አገር የትምህርት ዕድል አግኝቶ ስለሄደ ያደኩት ፍቅር በተሞላበት የአያቶቼ ቤት ነበር፡፡

ትምህርት ቤት ከገባሁ በኋላ አስተማሪዎቼ ለጥበብ ያለኝን ፍላጎትና ተሰጥኦ የተረዱት ገና ታዳጊ እያለሁ ነበር፡፡ ገና በ13 ዓመቴ እኔን ለሌሎች ምሳሌ በማድረግ የአማርኛ አስተማሪዬ ግጥሜን ለተማሪዎች ድምጹን ከፍ አድርጎ አንብቦልኛል፡፡ በዚያው ዓመት በየክፍለ ሀገሩ እየዞረ ለሚያሳየው ቲያትር ተማሪዎችን ይመለምል የነበረው የሙዚቃ አስተማሪዬ መላኩ አሻግሬ በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት እንድተውን እድል ሰጠኝ፡፡ ከዚያው ቲያትር ቤት በነበረ የአማተር ክበብ ውስጥም አባል ሆንኩኝ፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኜ ነው በትምህርት ቤታችን ባለው እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ የጀመርኩት ፤ የ11ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ለአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተዘጋጀ ስነ-ፅሁፍ ውድድር

ትምህርት ቤቴን በመወከል ተወዳድሬ አንደኛ ወጥቻለሁ፡፡ ይህንንም ተከትሎ የትምህርት ቤቴ የተማሪዎች ማህበር ምክትል ፕሬዝዳንት ሆኜ በመመረጤ ከሁለተኛ ደረጃና ከዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መሪዎች ጋር ትስስር የመፍጠር እድል አገኘሁ፡፡ ለዲሞክራሲና ለሴቶች መብት የመሟገት የእድሜ ልክ ትግሌ የጀመረው በዚህ መልኩ ነበር፡፡

በ18 ዓመቴ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ካጠናቀቅሁ በኋላ በብሄራዊ ቲያትር ለሁለት ዓመት ይሰጥ በነበረው አዲስ ስልጠና ፕሮግራም ውስጥ ከተካተቱት 12 እጩዎች መካከል አንዷ ሆኜ ለመመረጥ በቃሁ፡፡ ይህንንም ስልጠና በበላይነት ይመራ የነበረው አስደማሚው ባለ ቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ነበር፡፡ ለቀጣዩ 17 ዓመታትም በተዋናይነትና በፀሀፊነት መስራቱን ገፋሁበት፡፡

በሀገር ውስጥ ቲያትሮች ብቻ ሳይሆን ዘመን አይሽሬ በሆኑ የጥንት የውጭ ደራሲያን ተፅፈው በሀገራችን ሰዎች የተተረጎሙ ቲያትሮች ላይም ድንቅ ገጸ ባህሪያትን በመወከል ተጫውቻለሁ፡፡ በየቬኑስ ነጋዴ (ፖርትያን)፣ በሀምሌት (አፊሊያን) እንዲሁም በኒኮላይ ጎጎል ዋናው ተቆጣጣሪ (ማርያን) ሆኜ ለመተወን በመቻሌ ነፍሴ በሀሴት ጮቤ ረግጣለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በርካታ የግጥም ስራዎችን አበርክቻለሁ፡፡ ከነዚህ የግጥም ስራዎች መካከል የህፃናት አምባ ህጻናት የዘመሩት “ፀሀዬ ደመቀች” እና “ኢትዮጵያ” የሚለው የጥላሁን ገሰሰ ስራ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከፃፍኳቸው ግጥሞች መካከል አንዱን ልጋብዛችሁ፡፡

## የማታ እንጀራ ስጠኝ!

የማታ እንጀራ ስጠኝ፣

የጠዋት አታስመርጠኝ፣

ዘግይተህ በኋላ አስጊጠኝ፣

ማታ በክብሬ ደብቀኝ፣

ከሰው በር አንተው አርቀኝ...፣

አንገቴ እንዳለ ቀና ፣

የወዳጅ ደጃፍ ሳልጠና፣

"ዘራፍ!" እንዳልኩኝ ያብቃልኝ፣

ሲጨልም መንገድ አቅናልኝ፣

አደራ! ጌታዬ አደራ!

አትንሳኝ የማታ እንጀራ! (ተቀንጭቦ የተወሰደ)

*ተማሪዎች እስካሁን ከተነበበው የአለም ፀሀይ ወዳጆ ታሪክ ምን አዲስ እውቀት አገኛችሁ? በቀጣዩስ ክፍል ምን አዲስ ነገር የሚነሳ ይመስላችኋል?

ከዚህ በተጨማሪ ሴቶችና ህፃናትን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ በማተኮር በርካታ ስራዎችን ሰርቻለሁ፡፡ ለምሳሌ ወላጆቻቸው የጦርነት ሰለባ የሆኑባቸው ህፃናት በነበሩበት የዝዋይ የህፃናት አምባ ውስጥ የኪነ ጥበብ ፕሮግራሞችን በየአስራ አምስት ቀኑ በበጎ ፈቃደኝነት እያካሄድኩ እስከ 1982 ዓ.ም ድረስ ዘልቄአለሁ፡፡ ከሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመተባበር ደግሞ የኢትዮጵያ ተዋንያኖች ማህበርን

መስርቻለሁ፡፡ ማህበሩን በሊቀመንበርነት ባገለገልኩባቸው 14 ዓመታት ውስጥ በርካታ አስተዋጽኦዎችን አድርጌአለሁ፡፡

ከልቤ የምወደውን የኪነ ጥበብ ስራ በስፋት የመስራት ዕድል ያገኘሁት ግን በ1992 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ ጣይቱ የባህል ማዕከልን በማቋቋም በዋና አስተዳዳሪነት መምራት ስጀምር ነው፡፡ በአሜሪካ የመጀመሪያውን የአማርኛ ቤተ መጽሀፍት በዋሽንግተን ዲሲ ከፍተናል፡፡

ለታዳጊ ህፃናት የማስተላልፈው ምክር ግልፅና ቀላል ነው፡፡ ይሄውም "በራሳችሁ ተማመኑ፣ ትልቅ ነገር አልሙ፣ ጠንክራችሁ ስሩ፣ በምንም ዓይነት ሁኔታ ቢሆን ተስፋ አትቁረጡ" የሚል ነው፡፡

ምንጭ፡- (ተምሳሌት፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበር ቅንጅት ካሳተመው ፣ ገፅ፣ 123-125 ለክፍሉ እንዲመች ተሻሽሎ የቀረበ)

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (እንደ አስፈላጊነቱ)

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡-

ተግባር ሁለት፡-

ካዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ የተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ችሎታ (መክሊት)
2. ምልምል
3. በጊዜ ብዛት የማይቀየር
4. ተጎጂ
5. ገፀ-ባህሪያትን ተላብሶ መጫወት
6. ድጋፍ (ድርሻ)
7. መከራከር
8. በጣም ተደሰተች
9. ችሎታ
10. መንደር (ሰፈር)

ክፍል ሁለት፡- መናገር

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ የቀረበውን የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ እንዲያነቡና ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡
- ✓ ናሙና የሚሆን የሕይወት ታሪክ አዘጋጅተው ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሁለት


- ✓ የቀረበውን ሰንጠረዥ መሰረት በማድረግ የዶ/ር ሀዲስ አለማየሁን የሺጥላን የሕይወት ታሪክ በማቀናጀት አጠር አድርገው ንግግር እንዲያደርጉ ያግዟቸው፤ ድጋፍም ይስጧቸው ::

ምዘና፡-

- የህይወት ታሪክ መመሪያን ተገንዝበው በቅደም ተከተል መዘርዘራቸውን ያረጋግጡ
- የቀረበውን ሰንጠረዥ መሰረት በማድረግ የዶ/ር ሀዲስ አለማየሁን የሕይወት ታሪክ በማቀናጀት አጠር አድርገው በንግግር ማቅረባቸውን ያረጋግጡ።

መርጃ መሳሪያ፡-

- የአንድ ታዋቂ ሰው ናሙና የሕይወት ታሪክ የሚያሳይ ቢጋር



## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ

ቅድመ ንባብ

ተግባር

- ✓ ርዕሱን ካስተዋወቁ በኋላ ተማሪዎች ወደ ማንበብ ሂደት ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ። የተማሪዎችንም ምላሽ ይቀበሏቸው።
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ጥያቄ ያንብቡላቸው፤ስለ ስዕሉም ገለፃ ይስጧቸው።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

- ✓ ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ድረስ ያሉትን አንቀፆች ተማሪዎች እንዲያነቡና ለንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

- ✓ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲያነቡ ይዘዟቸው፤ ሁሉም ተማሪዎች ትኩረታቸውን ንባቡ ላይ ማድረጋቸውን ይከታተሉ፡፡

አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት እያሉ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡

ተግባር ሶስት

- ✓ በትዕዛዝ መሰረት የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብ እና በጥንድ በመወያየት ከምንባቡ ውስጥ ያሉ ፈሊጣዊ ንግግሮችን ካወጡ በኋላ በፍቻቸው ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፤ ግብረ መልስም ይስጡ፡፡

ምዘና፡-

- ምንባቡን በተገቢው መንገድ ማንበባቸውን ይከታተሉ
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታቸውን ያረጋግጡ
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡-

ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ሀሰት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. እውነት
6. ሀሰት

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ከምንባቡ የወጡት ቃላት በ "ለ" ስር ካለው ተቃራኒ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

1. መ
2. ሐ
3. ሠ
4. ሀ
5. ረ

ተግባር ሶስት፡-

ከታች የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብ እና በጥንድ በመወያየት ከምንባቡ ውስጥ ያሉትን ፈሊጣዊ ንግግሮችን ካወጣችሁ በኋላ በፍቻቸው ላይ ተወያዩ፡፡

1. ፋና ወጊ - ጀማሪ
2. ፈር ቀዳጅ - የመጀመሪያ
3. ፀጉረ-ልውጥ - እንግዳ (አዲስ)
4. “ሀ” ብሎ - አንድ ብሎ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

- ✓ የቀረበውን ማስታወሻ አንብበው በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከተወያዩ በኋላ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- ✓ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያን በመከተል የራሳቸውን ወይም አንድ የቅርብ ቤተሰባቸውን ሰው የህይወት ታሪክ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

ምዘና፡-

- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ዐረፍተ ነገር መመስረታቸውን ያረጋግጡ
- መመሪያውን ተከትለው የህይወት ታሪክ መፃፋቸውን ይመልከቱ

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ተግባር አንድ

✓ በምዕራፍ አንድ የተማሩትን ተዘውታሪ ቃላትን በተመለከተ ክለሳ ከተሰጣቸው በኋላ በትዕዛዙ መሰረት ዐረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት፡-

✓ በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው እንዲያስገቡ ያግዟቸው፡፡

ምዘና፡-

- በትዕዛዙ መሰረት ዐረፍተ ነገር መመስረታቸውን ይመልከቱ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡-

ተግባር ሁለት፡-

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ውሃ በላው | 6. የሞቀ ቤት |
| 2. ስራ ፈት | 7. አፈ ቅቤ |

3. ቅስሙ ተሰበረ
4. ገፀ በረከት
5. ልብ አቁስል
8. ሀሞቱ ፈሰሰ
9. ቂም አርግዛለች
10. አመድ አፋሽ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ ከስር የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎች ካነፏቸው በኋላ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ስማዊ ሀረጎች እንዲያወጡ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ተግባር ሁለት ላይ የተሰጡትን ስማዊ ሀረጎች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፤ እርማትም ይስጡ፡፡

ማስታወሻ፤

**ሀረግና የሐረግ መዋቅር**

ሀረግ ማለት ትርጉም ያላቸው ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው፡፡ አምስት የቃል ክፍሎች ማለትም ስም፣ ቅጽል፣ ግስ፣ ተውሳከ ግስ እና መስተዋድድ እያንዳንዳቸው ከሌሎች ተዋቃሪዎች ጋር በመቀናጀት ሀረግ ይመሰርታሉ፡፡ የሀረጉም ዓይነት በሀረጉ ውስጥ ዋና ሆኖ በሚገባው ቃል ዓይነት ይወሰናል፡፡ ዋናው ቃል ሆኖ የሚገባው ቃል የሀረጉ መሪ ይባላል፡፡

በዚህም መሰረት ከስም ስማዊ ሀረግ፣ ከቅጽል ቅፅላዊ ሀረግ፣ ከግስ ግሳዊ ሀረግ፣ ከተውሳከ ግስ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ፣ ከመስተዋድድ

መስተዋድዳዊ ሀረግ እንመሰርታለን፡፡

ሀ. ስማዊ ሀረግ፡- ስማዊ ሀረግ ስሞችን ቀኝ መሪ አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- የጨርቅ ኳስ

የሀረር ብርቱካን

ለ. ቅጽላዊ ሀረግ፡- የሀረጉ መሪ ቅፅል ከሆነ ሀረጉ ቅፅላዊ ሀረግ ተብሎ ይጠራል፡፡

ምሳሌ፡- በጣም ጎበዝ

እንጨት ሰባሪ

ሐ. ግሳዊ ሀረግ፡- ግሶችን ቀኝ መሪ ያደረገ የሀረግ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ወደ ሀረር ሄደ፡፡

በፍጥነት መጣ፡፡

መ. ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ፡- ተውሳከ ግሶችን ቀኝ መሪ ያደረገ የሀረግ መዋቅር ነው፡፡

ምሳሌ፡- በጣም በፍጥነት

ቁልቁለቱን ቶሎ

ሠ. መስተዋድዳዊ ሀረግ፡- መስተዋድዳዊ ሀረግ መስተዋድዶች በስም፣ በግስ እንዲሁም በተውሳከ ግስ የቃል ክፍል ውስጥ ከሚመደቡት ቃላት ጋር ቀኝ ወይም ግራ መሪ ሆነው በመቀናጀት የሚፈጥሩት የሀረግ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- እንደ ወንድሜ

እናቴ ወደ

ምዘና፡-

- በተሰጡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የቀረቡትን ስማዊ ሀረጎች መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ
- የተሰጡትን ስማዊ ሀረጎች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች መመስረታቸውን ያረጋግጡ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማስታወሻና መመሪያ መሰረት ከታች ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ስማዊ ሀረጎች አውጡ፡፡

ሀ. የስንዴ ዳቦ

ለ. የታመመው ልጅ

ሐ. ጎበዝ ተማሪ

መ. ጥቁር እስክርቢቶ

ሠ. የሐረግ ሹራብ

# ምዕራፍ አምስት (፭)

## ውሃና ጥቅሙ

(ክፍለ ጊዜ 9)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- ➢ ከሚደመጡ ንግግሮች ውስጥ ማስታወሻ ይይዛሉ።
- ➢ ስለውሃ ጥቅም ይገልጻሉ።
- ➢ የራሳቸውን ዝንባሌና ፍላጎት ይገልፃሉ።
- ➢ በርካታ ቃላትን ይዘረዝራሉ።
- ➢ የውሃ አይነቶችን ይዘረዝራሉ።

### የትምህርት ይዘቶች

- አድምጦ መረዳት
- መረጃ መጠየቅ
- ምክንያትና ውጤት
- ተራኪ ጽሁፍ
- እማሬያዊ ፍቺ
- ገቢርና ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው፡፡
- ✓ በቅድመ ማዳመጥ ላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ስለውሃና የውሃ ጥቅም የማውቀው እና የማላውቀው የሚለውን ረድፍ ተማሪዎቹ በተናጥል እንዲሞሉት ያድርጉ፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉየምንባቡን ቅጅ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ መሙላታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ክፍተቱን ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡

### የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር

- ✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ፡፡

- ✓ በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በምልክት ቋንቋ ታግዘው ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ ከዚያም የቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡

አድምጦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ተማሪዎቹ ወደ ሰንጠረዡ ተመልሰው ከምንባቡ ስለውሃና የውሃ ጥቅም ያወቅሁት የሚለውን ረድፍ እንዲሞሉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶቻቸውን በእርሶ መሪነት እንዲመርጡ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሶስት

- ✓ በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ቁልፍ ቃላት በቀረቡት ያልተሟሉ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው እንዲያስገቡ ያድርጓቸው፡፡

## "ውሃና የውሃ ጥቅም"

"የውሃ እና የእናት መጥፎ የለውም" የሚል ሀገራዊ ብሂል አለ፤ በተቃራኒው "ውሃማ የጥቅምት ነበርሽ፣ ግን ማን በጠጣሽ" የተባለለት የውሃ ዓይነት አለ፡፡ ውሃ ከሚገኝበት አንጻር የምንጭ፣ የሀይቅ፣ የኩሬ፣ የወንዝ፣ የቧንቧ፣ የዝናብ፣ የውቅያኖስና የባህር ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

ሁሉም ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት ለመኖር ውሃ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ሁለት ሶስተኛ የሚሆነው የሰውነታችን ክፍል በውሃ የተገነባ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ ፈሳሽ በተለይ በደማችን በምራቃችን በቆዳችን ወዘተ ውስጥ የተከማቸ ነው፡፡ ውሃ ለሰው ልጅ ያለው ጠቀሜታ በርካታ ነው፡፡ ለምሳሌ፦ የምግብ መፈጨት ስርዓት ያለ ውሃ ስራውን በትክክል ማከናወን አይችልም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አንደ ኦክስጅንና አልሚ ንጥረ ነገሮችን በትክክል ማጓጓዝ፤ ጥሩ የደም ዝውውር ወይም የሰውነት ሙቀት መጠንን ማስተካከል እንዲቻል በሰውነት ውስጥ ውሃ ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ አንጎላችን ሰባ ሁለት በመቶ የተሰራው ከውሃ ስለሆነ በብዛት መጠጣት የአዕምሮ ስራን ያሻሽላል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የእለት ተእለት ድካሞቻችን ዋና ምክንያት በቂ የሆነ ውሃ አለመጠጣት ነው፡፡ ስለዚህ ለውሃ እንክብካቤ ማድረግ (ጥራቱን መጠበቅ) የመጀመሪያ ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከተነበበው ምንባብ በመነሳት ውሃ ለሰው ልጅ ምን ምን ጠቀሜታ እንዳለው ተናገሩ፡፡ ውሃ በምን በምን ምክንያቶች ሊበከል እንደሚችል ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡*

ጎጂ ተዋህሲያንና ንጥረ ነገሮች ውሃማ አካላትን ይበክላሉ፤ የውሃ ጥራት እንዲቀንስ ያደርጋሉ፤ ከዚህ በተጨማሪ ውሃን መርዛማ ያደርጉታል፡፡ ውሃ በህይወት ለመኖር ከሚጠቅሙ ንጥረ ነገሮች አንደኛው ቢሆንም እንዳለመታደል ሆኖ ግን ለብክለት በጣም የተጋለጠ ነው፡፡

ውሃን የሚበክሉ በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ እነሱም ፡- ከፋብሪካ የሚወጡ ጽዳጆች፣ በባህር ላይ የሚጣሉ ቆሻሻዎች፣ ከመኖሪያ ቤቶች የሚወጡ ፍሳሾች፣ የአረምና የተባይ ማጥፊያዎች... የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የውሃ ብክለት በጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል፡፡ በተባበሩት መንግስታት መረጃ መሰረት በየ ዓመቱ በውሃ መበከል ምክንያት የሚከሰተው ሞት በጦርነት እና በተለያዩ ግጭቶች ከሚሞቱ ሰዎች ቁጥር ይበልጣል፡፡ ከሰዎችና ከእንስሳት የሚወጡ ጽዳጆች ውሃን ይመርዛሉ፡፡ ውሃው ደግሞ የተለያዩ ባክቴሪዎችንና ቫይረሶችን ይይዛል፡፡ እነዚህ ቫይረሶችና ባክቴሪያዎች ደግሞ ለበሽታ መዛመት ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ ለምሳሌ ታይፎይድ፣ ኮሌራና ጃርዲያ ውሃ ወለድ በሽታዎች ናቸው፡፡

የውሃ ብክለት በአካባቢ ስነ-ምህዳር ላይ ትልቅ ጉዳት ያደርሳል፡፡ እንስሳት ምቹ የሆነ መኖሪያ እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢኮኖሚ ላይ በርካታ ጉዳቶች ያደርሳል፡፡ ከዚህም ውስጥ በዓሳ ማጥመድ፣ በመዝናኛ ቦታዎች፣ በቱሪዝምና በሌሎች ተቋማት ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡ ምክንያቱም የሁሉም እንቅስቃሴ ከንጹህ ውሃ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ስላለው፤ እንዲሁም የተበከለን ውሃ ለማከም ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የንጹህ መጠጥ ውሃን ዋጋ ከፍ ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ ውሃ ከዕለት ተዕለት ኑሮችን ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለው አውቀን በአግባቡ መጠቀምና እንክብካቤ ማድረግ፤ ስለውሃ አጠቃቀም ለማህበረሰቡ ማስተማር ወዘተ. ይጠበቅብናል፡፡

ምንጭ፡- (ኢስት ሴንትራል ዩኒቨርሲቲ ከ ገጽ 25-30 ለማስተማሪያ ከተዘጋጀ ሰነድ ላይ ለክፍሉ እንዲመጥን ተደርጎ የተተረጎመ፡፡)

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (እንደ አስፈላጊነቱ)
- የውሃን ጠቀሜታ በዝርዝር የሚያሳይ ቻርት

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡-

ተግባር አንድ፡-
ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. መ
2. መ
3. መ
4. ሐ
5. ለ
6. ሀ

ተግባር ሁለት፡-
በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

1. ሠ
2. መ
3. ቀ
4. ሐ
5. ሸ
6. ለ
7. ረ

ተግባር ሶስት፡-

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የተሰጡትን ቃላት በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው አስገቡ።

1. ተዋህሲያን
2. አልሚ
3. መዛመት
4. ያሳያሉ
5. ብሂል
6. አንፃር

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

✓ ውሃና ጥቅሙ በሚል ርዕስ ካዳመጡት ምንባብ የወሰዱትን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ስለውሃ አይነቶች እና ጠቀሜታ ውይይት እንዲያደርጉ ያግዟቸው።

ተግባር ሁለት

✓ በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ያላቸውን አመለካከትና ፍላጎት በተመለከተ በምክንያትና ውጤት አስደግፈው እንዲናገሩ ያድርጓቸው።

ምዘና፡-

- ውሃን በተመለከተ ያላቸውን የግል አመለካከት በምክንያትና ውጤት አስደግፈው ማቅረባቸውን ያረጋግጡ።

መርጃ መሳሪያ፡-

- የምክንያትና ውጤት ተዛምዶን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ንባብ

### ተግባር

✓ ተማሪዎች ወደ ማንበብ ሂደት ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ የተማሪዎችንም ምላሽ ይቀበሏቸው፡፡በክፍል ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎችካሉ ጥያቄውን እንዲያንቡላቸው ያድርጉ፤ስለ ስዕሉም ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

### የማንበብ ሂደት

✓ ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ያሉትን አንቀፆች ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ ፡፡

✓ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲያነቡ ይዘዟቸው፤ ይከታተሏቸው፡፡

### አንብቦ መረዳት

### ተግባር አንድ

✓ "ለውሃ ስም አነሰው" በሚል ርዕስ ባነበቡት ምንባብ መሰረት የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በፅሁፍ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ድጋፍም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ለቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሶስት

- ✓ ለተማሪዎቹ ስለምክንያትና ውጤት ዝምድና ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም ምሳሌዎቹን መሰረት በማድረግ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ምክንያትና ውጤቶች በመለየት እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

## ምክንያትና ውጤት

### ማስታወሻ

ምክንያት የምንለው አንድ ነገር ለመከሰቱ መንስኤ ወይም ሰበብ የሆነው ነገር ሲሆን፣ በክስተቱ ሳቢያ የሚገኘው ግብ ደግሞ ውጤት ይባላል፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ባህሌን ጠብቄ በመኖሬ ደስተኛ ነኝ፡፡

ምክንያት = ባህሌን ጠብቄ በመኖሬ

ውጤት = ደስተኛ ነኝ

ተግባር አራት

- ✓ በውሃ ወለድ ስለሚተላለፉ በሽታዎች ምንነትና ስለሚያስከትሉት ጉዳት ከቤተሰቦቻቸው፣ ከአካባቢያቸው ወይም ከቤተ መፃህፍት መረጃ ሰብስበው በመምጣት በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- ምንባቡን በተገቢው መንገድ ማንበባቸውን ይከታተሉ
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠታቸውን ይከታተሉ
- በስርዓት መወያየታቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- አውዳዊ ፍቺን የሚያሳይ የቃላት ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡-

## ተግባር ሁለት፡-

ከታች ለቀረቡት ካነበባችሁት ምንባብ የወጡ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የከበረ (የያዘ)
2. ማፍለቅ
3. ሰብል
4. አሳ አጥማጆች
5. ሲቆጨኝ
6. ቆሻሻዎች
7. መመረዝ
8. አላግባብ መጠቀም

ተግባር ሶስት፡-

መምህራችሁ በሰጧችሁ ማስታወሻ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በማንበብ ምክንያትና ውጤታቸውን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

1. ምክንያት = በሙስና መጠርጠር

   ውጤት = በፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋል

2. ምክንያት = የራስ ህመም

ውጤት = ከትምህርት ቤት መቅረት

3. ምክንያት = ውሃን በአግባቡ አለመያዝ

ውጤት = ለተለያዩ በሽታዎች መጋለጥ

4. ምክንያት = ቤተሰብ አልባ መሆን

ውጤት = ትምህርቱን ማቋረጥ

5. ምክንያት = ጠንክሮ መስራት

ውጤት = ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ

6. ምክንያት = ጥንቃቄ አለማድረግ

ውጤት = የኮሮና መስፋፋት

7. ምክንያት = ቶሎ ወደ ሆስፒታል አለመሄድ

ውጤት = የህይወት ማለፍ

8. ምክንያት = የአሽከርካሪዎችና የእግረኞች ቸልተኝነት

ውጤት = የትራፊክ አደጋ መስፋፋት

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ የማይረሱትን ገጠመኝ መሰረት በማድረግ ባለ ሁለት አንቀጽ ተራኪ ጽሁፍ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ በተግባር አንድ የፃፉትን ጽሁፍ በመቀያየር እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያግዟቸው፡፡

ምዘና፡-

- ባለ ሁለት አንቀፅ ተራኪ ጽሁፍ መፃፋቸውንና መተራረማቸውን ያረጋግጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡-

- ተራኪ ጽሁፍን የሚያሳይ ሞዴል አንቀፅ

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ በመምህሩ መምሪያ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡ ማስታወሻውን ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲያነቡ ያድርጓቸው፤ ማብራሪያም ይስጧቸው፡፡

- ✓ በማስታወሻው በቀረበው ምሳሌ መሰረት ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ከላይ ፍቺ በሰጡባቸው እማሬያዊ ቃላት ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱባቸው ያድርጉ፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## የቃላት እማሬያዊ ፍቺ

### ማስታወሻ

ቃላት የተለያዩ ፍቺዎች አሏቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

እማሬያዊ ፍቺ ማለት የአንድ ቃል ጥሬ ትርጉም ወይም የመዝገበ ቃላት ፍቺው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ እማሬያዊ ፍቺ የቃሉ ቀጥተኛ ፍቺ ነው እየተባለ ይገለፃል፡፡

| ምሳሌ፡- | ቃል | እማሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|
| | በግ | ሳር በል የቤት እንስሳ |
| | ውሻ | ስጋ በል የቤት እንስሳ |
| | እርግብ | በራሪ የወፍ ዝርያ |
| | ጉቶ | መሬት ላይ የቀረ ጉራጅ እንጨት |

ምዘና፡-

- ለቀረቡት እማሬያዊ ቃላት ፍቺ መስጠታቸውንና ዓረፍተ ነገር መመስረታቸውን ያረጋግጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡-

- የቃላትን እማሬያዊ ፍቺ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማስታወሻና ማብራሪያ መሰረት ከታች ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የሚያቃጥል የበርበሬ ዘር
2. የንብ መኖሪያ
3. ማር የምትሰጥ በራሪ ነፍሳት
4. መለኪያ
5. የቤት እንስሳ
6. ምድር
7. ብርሃን ያልሆነ (ሌሊት)
8. ዶሮ መሰል ስጋዋ የሚበላ የወፍ ዘር
9. ውሃማ አካል
10. መቀመጫ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ተግባር አንድ

- ✓ በቀረበው ማስታወሻ መሰረት ተማሪዎች እንዲወያዩ ካደረጉ እና ግብረ መልስ ከሰጧቸው በኋላ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ገቢርና ተገብሮ በማለት ለይተው እንዲጽፉ ያድርጓቸው።

### ተግባር ሁለት

- ✓ አምስት የገቢር ዓረፍተ ነገር ከመሰረቱ በኋላ ወደ ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች እንዲለውጡ ያድርጓቸው።

ምዘና፡-

- ገቢርና ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮችን መለየታቸውን ያረጋግጡ።
- ገቢር ዓረፍተ ነገሮችን ወደ ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች መለወጣቸውን ያረጋግጡ።

መርጃ መሳሪያ፡-

- ገቢርና ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

### በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ገቢርና ተገብሮ በማለት ለይታችሁ ፃፉ።

| | |
|---|---|
| 1. ገቢር | 6. ገቢር |
| 2. ተገብሮ | 7. ገቢር |
| 3. ተገብሮ | 8. ተገብሮ |
| 4. ገቢር | 9. ገቢር |
| 5. ተገብሮ | 10. ተገብሮ |

# ምዕራፍ ስድስት (፮)

## የሰዎች ዝውውር

(ክፍለ ጊዜ 9)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- ካዳመጡት ነገር በመነሳት ዋናውን ሀሳብ ይገልፃሉ።
- የሰዎችን ዝውውር ጽንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ።
- ከጓደኞቻቸው ጋር በራስ በመተማመን ንግግር ያደርጋሉ።
- በትክክል ያነባሉ።
- የሰዎች ዝውውር የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ያብራራሉ።

**የትምህርት ይዘቶች**

- አድምጦ መተንተን
- ከጓደኛ ጋር መነጋገር
- አቀላጥፎ ማንበብ
- ፍካሬያዊ ፍቺ
- የዓረፍተ ነገር አይነቶች

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው።
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው።
- ✓ "ያመቻል" በሚሉት መንገድ ተማሪዎች ቡድን እንዲመሰርቱ አድርገው በቅድመ ማዳመጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፤ ምላሻቸውንም ይቀበሏቸው።
- ✓ ከየቡድኖቹ በውይይት የደረሱበትን መደምደሚያ በመቀበል ያለውን የእውቀት ክፍተት ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው።

### የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር

- ✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው።
- ✓ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ።
- ✓ የቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፤መስማት የተሳነው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካለ የምንባብ ቅጅ እንዲደርሳቸው ያድርጉ።

አዳምጦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች በጽሁፍ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ካዳመጡት ምንባብ የወጡትን ቃላትና ሀረጋት ከተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡

## "ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር"

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶችም ለስራ፣ ለትምህርት፣ ለንግድ፣ ለመዝናናት፣ ለህክምና፣ ለተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወዘተ. ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ፡፡ ይህንንም እንቅስቃሴ ህጋዊና ህገ-ወጥ ብለን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ በህጋዊ መንገድ የሚከናወነው የሰዎች ዝውውር የሚደግፍና በህግ አካላትአውቅና ያለው ሲሆን፣ በህገ-ወጥ መንገድ የሚደረገው የሰዎች ዝውውር ምንም አይነት ህጋዊ መንገድን ያልተከተለ መንገደኞች ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው የሚፈጽሙት ተግባር ነው፡፡

ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ማለት ሰዎችን በግድ ወይም በማስፈራራት ጠልፎ፣ አጭበርብሮ፣ አታሎ ወይም በሌሎች መንገዶች መመልመል፣ ማዘዋወር፣ ማቆየት ሲሆን ይህም የግዳጅ ስራ ለማሰራት የሚደረግ ሂደት ነው፡፡ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተስፋፋ ይገኛል፡፡ ህገ-ወጥ ዝውውርን በተመለከተ በዓለም ላይ ያሉ ሀገሮችን የዝውውር ምንጭ፣ መተላለፊያና መድረሻ በማለት በሶስት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ ምንጭ የሚባሉት ተጠቂዎች በመጀመሪያ

የሚመጡባቸው አገሮች ናቸው። በአብዛኛው በተጠቂዎች ላይ አደጋ የሚደርሰው መተላለፊያ አገሮች ላይ ሲሆን መተላለፊያዎች ተጠቂዎች የሚያቋርጧቸው ሀገሮች ናቸው። መድረሻ ሀገሮች ደግሞ ተጠቂዎች በመጨረሻ ለስራ፣ ለጉብኝት ወይም ለትምህርት መሄድ የሚፈልጉበት ሀገሮች ናቸው።

ለህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት፣ ሴቶችና ልጆች፣ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ሰዎች፣ በቂ ትምህርትና አስታውሎት የሌላቸው ሰዎች፣ ስለ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ያልሰሙ ወይም የማያውቁ ሰዎች፣ በችግር ላይ ሆነው ራሳቸውን ለማሻሻል እየሞከሩ ያሉ ሰዎች፣ ከአገር ለመውጣት ሲያስቡ ጓደኛ ወይም ቤተሰብ የሚሉትን በጭፍን የሚያምኑ ሰዎች፣ የራሳቸውን ወይም የቤተሰቦቻቸውን ንብረት ሸጠው ወይም ተበድረው ወደ ውጭ አገር መጓዝ የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው።

*ተማሪዎች እስካሁን ከተነበበው ምንባብ በመነሳት ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ማለት ምን ማለት ነው? ሰዎች ለምን በህገ-ወጥ መንገድ ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ ይመስላችኋል?

## የህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያቶች፡-

በአካባቢያቸው የነበሩ ሰዎች ውጭ ሀገር ሄደው ሰርተው በመመለስ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ኑሮ ሲያሻሽሉ መመልከትና ለቤተሰቦቻቸው በሚልኩት ገንዘብ መማረክ፤ እንዲሁም ለተጎጂው ቅርብ የሆነ የቤተሰብ አባልና ጓደኛ ተጎጂው ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ እንዲሰራ ጫና መፍጠር ሰዎችን በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መረብ ውስጥ እንዲገቡ እንደሚያደርጋቸው ጥናቶች ያመለክታሉ።

ህገ ወጥ ደላሎች የሚሰጡት ሀሰተኛ መረጃና ተስፋ ደግሞ ለዚሁ አደጋ አንዱ በር ከፋች ነው፡፡ ህገ ወጥ ደላሎች በዚህ ድርጊት ውስጥ የሚያገኙት ጥቅም እጅግ በጣም የተጋነነ ከመሆኑ የተነሳ ሰዎችን ለመመልመልና ልባቸውን ለማነሳሳት በቀላሉ ሊታወቁ የማይችሉ ውስብስብ ስልቶችን ይጠቀማሉ፡፡ በመሆኑም ሰዎችን የሀሰት ተስፋና መደለያ በመስጠት ወደ ውጭ ሀገር ቢሄዱ ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው የሚተርፍ ሀብት ማፍራት እንደሚችሉ የማባበያ ስራ ይሰራሉ፡፡

ሌላውና የመጨረሻው ደግሞ ዜጎች ለተሻለ ህይወት ፍለጋ ሲሉ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለህገ ወጥ ሰዎች ዝውውር መበራከት መሰረት ሊሆን እንደቻለ ይታመናል፡፡ ዜጎች ያሉበትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የኑሮ ሁኔታቸውን ለማሻሻል ሲሉ የተሻለ የስራ እንቅስቃሴና የኢኮኖሚ አቅም ወዳለበት ሀገር ለመጓዝ በሚያደርጉት ጥረት ለአደገኛ የሰዎች ዝውውር እንደሚጋለጡ ይነገራል፡፡

## ከህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እንዴት ራስን መጠበቅ ይቻላል?

ከህገ ወጥ ደላሎች ራስን መጠበቅ፣ ከደላሎች የሽንገላ ምክር ራስን ማዳን፣ ለተማሪዎችና ለማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ውስጥ በተለይ በስደት ወቅት ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች በመጠቀም ተሞክሯቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፤ በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችን ቁጥጥር በማድረግ ለህግ በማቅረብ አስፈላጊውን አርምጃ መውሰድ፤ ለወጣቶች በየአካባቢያቸው የስራ እድል በመፍጠር ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን መከላከል ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገራት እየተስፋፋ የመጣ ስለሆነ ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ራሳችንንና ቤተሰቦቻችንን ከዚህ ህገ ወጥ ተግባር መጠበቅ ይኖርብናል፡፡

ምንጭ፡- ጂ አይ ዜድ (GIZ) የጀርመን የተራዶ ድርጅት ፣2020፣ የታተመ፡፡

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- ስለ ሰዎች ዝውውር ምንነትና ጉዳት ይጠይቋቸው

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (እንደ አስፈላጊነቱ)

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቾቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

1. ሸ
2. ሰ
3. በ
4. ሀ
5. ለ
6. መ
7. ረ
8. ቀ
9. ሠ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### የትምህርቱ አቀራረብ

✓ የሰዎች ዝውውር ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ በቡድን ከተወያዩ በኋላ የደረሱበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፤ ድጋፍና ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- በራስ በመተማመን ሀሳባቸውን መግለፃቸውን ያረጋግጡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ንባብ

### ተግባር

- ✓ ርዕሱን ያስተዋውቋቸው፤ በቅድመ ንባብ በቀረቡት ቃላት ፍቺ ዙሪያ ከጓደኞቻቸው ጋር ከተወያዩ በኋላ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው።
- ✓ አይነ-ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ ምንባቡን ያንብቡላቸው።

### የንባብ ጊዜ

### ተግባር

- ✓ ምንባቡን በየግላቸው እንዲያነቡ ያድርጓቸው።
- ✓ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲያነቡ ይዘዟቸው፤ ይከታተሏቸው።
- ✓ አይነ-ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ ምንባቡን ያንብቡላቸው።
- ✓በክፍል ውስጥ አይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ስለሰለሆ ማብራሪያ ይስጧቸው፤ጥያቄዎችንም ያንብቡላቸው።

### አንብቦ መረዳት

### ተግባር አንድ

- ✓ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል የሆኑትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ሀሰት በማለት በቃላቸው ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ እርማትም ይስጡ።

ተግባር ሁለት

✓ ለተሰጡት ቃላትና ሀረጋት ወደ ምንባቡ በመሄድ ተመሳሳይ ፍቻቸውን እንዲፈልጉ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሶስት

✓ ተማሪዎቹ ተራ በተራ እየወጡ የሶስቱ እንስት የስደት ታሪክ የሚለውን ምንባብ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያድርጉ፤ በሚያነቡበት ጊዜም የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ በትክክል ማንበባቸውን ይከታተሉ፡፡

### ማስታወሻ፤አቀላጥፎ ማንበብ

አቀላጥፎ ማንበብ ማለት ፊደላትን፣ ቃላትንና ሀረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጪ በሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ ነው፡፡ አንድን ጽሁፍ በትክክል አቀላጥፈን በምናነብበት ጊዜ የአቀላጥፎ ማንበብ መመሪያዎች መተግበር ተገቢ ነው፡፡ እነሱም፡-

1. ፅሁፉ ለምን ዓላማ እንደሚነበብ ማወቅ፤
2. መጥፎ የንባብ ልምድን ማስወገድ፡፡ እነሱም፡-
   - በምናነብበት ጊዜ ከንፈር ማንቀሳቀስ
   - ድምፅ ማሰማት
   - ጽሁፉን በጣት እየጠቆሙ ማንበብ ናቸው፡፡ እነዚህ ልማዶች የንባብ ፍጥነትን ይቀንሳሉ፡፡
3. ጽሁፉን ሲነበብ በሚችል ርቀት መያዝ፤
4. ጽሁፉ ሲበብ ዓይንን ብቻ ማንቀሳቀስ (የራስ ቅልን ማንቀሳቀስ ጥሩ ልምድ አይደለም)፤
5. ቃላትን ለየብቻ እየነጠሉ ከማንበብ ሀረጎችንና ዓረፍተ ነገሮችን አያይዞ ማንበብ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ምዘና፡-

- ምንባቡን አቀላጥፈው በትክክል ማንበባቸውን ያረጋግጡ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. እውነት
2. ሀሰት
3. ሀሰት
4. እውነት
5. ሀሰት

ተግባር ሁለት፡-

ከታች ለተሰጡት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከምንባቡ ውስጥ ካሉት አንቀፆች ፈልጉ፡፡

1. አሐዱ ብላ
2. ፀጋ
3. ራዕይ
4. ጥሪት
5. ውልፍት
6. እንግልት

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ ስለገላጭ ጽሁፍ ምንነትና ባህሪያት ተማሪዎች ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጉ፤ ተጨማሪ አስረጂ እንዲሆናቸው ከታች የቀረበውን ምሳሌ ያንብቡላቸው (ይጻፉላቸው)፡፡
- ✓ በቀረበው ቢጋር መሰረት ሁለት አንቀጽ ገላጭ ጽሁፍ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ አይነ-ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ ስለቢጋሩ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

የገላጭ ጽሁፍ ምሳሌ

ምሳሌ አንድ፡-

አስም ምንድን ነው? ምንም አይነት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሳያሳይ የትንፋሽ እጥረት ወይም መታፈን ሲያጋጥም ሰዎች አስም ተነሳባቸው እንላለን፡፡ በትንፋሽ መታፈን ምክንያት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየዓመቱ በሞት ይለያሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የአስም ጅማሮ ከእያንዳንዱ ሳል ጋር በተያያዘ ደረቅ ጉንፋን ይከሰታል፡፡

ምሳሌ ሁለት፡-

በሀገራችን የቱባ ባህል መገለጫ የሆነው ጋቢ በጎበዝ ሞያተኛ ሴት ተፈትሎ በድርና ማግ ተቀይጦ በሸማ ሰሪዎች የእጅ ጥበብ ተዋህዶ ከጥጥ የሚሰራ ባህላዊ ልብስ ነው፡፡ በአንድ ማህበረሰብ መልካም ስራ ለሰሩ ለሚያገቡና ለተመረቁ ሰዎች በብዛት በስጦታነት ይበረከታል፡፡

ጋቢ ነጠላና ድርብ ተብሎ በሁለት አይነት መልኩ ይዘጋጃል፡፡ ነጠላ ጋቢ በቀጭኑ ተፈትሎ በስሱ የሚሰራ ሲሆን ድርብ ጋቢ ደግሞ በወፍራሙ ተፍትሎ በድርቡ የሚሰራ ነው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ጥንድ ጥንድ በመሆን የፃፉትን ገላጭ ጽሁፍ በመቀያየር እንዲተራረሙ ያድርጓቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- የቀረበውን ቢጋር መሰረት በማድረግ ገላጭ ጽሁፍ መጻፋቸውን ያረጋግጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡-

- የገላጭ ፅሁፍ ሞዴል አንቀፅ

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ የቀረበውን የፍካሬያዊ ፍቺ ማስታወሻ ተማሪዎች አንብበው ውይይት ያድርጉ፡፡
- ✓ ማስታወሻውን ይስጧቸው፤ ገለፃም ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ በምሳሌው መሰረት ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሶስት

- ✓ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ጽፌው በፍቻቸው ዙሪያ ውይይት እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡

ምዘና፡-

- ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡-

- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

ከላይ በማስታወሻው በቀረበው ምሳሌ መሰረት ከታች ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የማይለቅ
2. ፈሪ
3. ረጅም
4. ተጣብቆ የማይለቅ
5. የማይረባ
6. ፈጣን
7. ሆዳም
8. ክፉ
9. ቀጭን
10. ልፍስፍስ

ተግባር ሁለት፡-

ቀጥለው በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ስራ
2. ጀግንነት
3. አታላይ
4. ነገር ጫሪነት (አያያዥ)
5. ጎበዝ
6. ባህሪው የማይጨበጥ
7. ወፍራም
8. ትዳሯን

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ተግባር አንድ

- ✓ ስለ ዓረፍተ ነገር ስልቶች የቀረበውን ማስታወሻ ይስጧቸው፤ ገለፃም ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ በማስታወሻው መሰረት የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በስልታቸው እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

### ተግባር ሁለት

- ✓ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የዓረፍተ ነገር ስልት ቢያንስ ሁለት ሁለት ዓረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱ ያድርጉ፤ እርማትም ይስጡ፡፡

ምዘና፡-

- የተለያዩ የዓረፍተ ነገር ስልቶችን ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር መመስረታቸውን ያረጋግጡ

### በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### ተግባር አንድ

ተማሪዎች ከላይ በተሰጠው ማስታወሻ ውስጥ የተሰጡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን የዓረፍተ ነገር ስልቶች ለዩ፡፡

1. ትዕዛዛዊ
2. መጠይቃዊ
3. ሀተታዊ (አዎንታዊ)
4. ሀተታዊ (አሉታዊ)
5. ሀተታዊ (አዎንታዊ)
6. ትዕዛዛዊ
7. መጠይቃዊ
8. ትዕዛዛዊ
9. ሀተታዊ (አዎንታዊ)
10. ሀተታዊ (አዎንታዊ)

# ምዕራፍ ሰባት (፯)

## ማህበራዊ ግንኙነት

(ክፍለ ጊዜ 12)

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣

- በጥልቀት ያዳምጣሉ።
- የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት ይገልፃሉ።
- በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ጽሁፍ ይፅፋሉ።
- ውስብስብ ዐረፍተ ነገር ይመሰርታሉ።

### የትምህርት ይዘቶች

- በአትኩሮት ማዳመጥ
- ከጓደኛ ጋር መወያየት
- የተለመዱ ፈሊጣዊ አገላለፆች
- በተወሰኑ ርዕሶች ላይ የሚዘጋጅ ጽሁፍ
- የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ
- ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው፡፡
- ✓ በቅድመ ማዳመጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፤ ምላሻቸውንም ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ከየቡድኖቹ በውይይት የደረሱበትን መደምደሚያ በመቀበል ያለውን የእውቀት ክፍተት ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የመስማት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ የምንባቡ ቅጅ ይስጧቸው፡፡

### የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

- ✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት የፈሊጣዊ ንግግር ፍቺን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ፡፡ ከዚያም የቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡

አዳምጦ መረዳት

ተግባር አንድ

✓ ማዳመጡ እንዳለቀ ወደ ተግባር አንድ በመሸጋገር ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ሁለት

✓ በምንባቡ መሰረት ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮችን በተገቢው መንገድ እንዲያሟሉ ያድርጉ፡፡ ግብረ-መልስም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሶስት

✓ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ ለተመሰረተባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡

"ጎፋ መስቃላ ዮ"

የጎፋ ብሄረሰብ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሰት ውስጥ ካሉት ሀምሳ ስድስት ብሄረሰቦች አንዱ ነው፡፡ ከመዲናዋ አዲስ አበባ በአምስት መቶ አስራ ስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን የራሱ የሆነ ቋንቋና የባህል እሴቶች አሉት፡፡ የአብዛኛው ህዝብ ኑሮ የተመሰረተውም በግብርና ላይ ነው፡፡

በጎፋዎች ቋንቋ የመስከረም ወር ጉስታማ ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ወር በማህበረሰቡ የጭፈራና የደስታ ወር ተብሎ ይጠራል፡፡ በዓሉን ለማክበር ከመስከረም አንድ ጀምሮ ዝግጅቱ ይጀምራል፡፡ ለዚህም ቅድመ ዝግጅቶች ይካሄዳሉ፡፡ ወንዶች የእርድ በሬ ለመግዛት ዓመቱን ሙሉ ሲቆጥቡ፣ ሴቶች ደግሞ ቡልኮ ለመስራት አመቱን ሙሉ ኡጋሪ የሚል ጥጥ ይፈትላሉ፡፡ የደመራው እለት እየተቃረበ ሲመጣም ወንዶች ለደመራ የሚውል የተመረጠ እንጨት ይሰበስባሉ፣ ለከብቶች

መኖም ያዘጋጃሉ። ህፃናቱም በዚህ በዓል ላይ የተለያዩ ግጥሞችን እያዜሙ በዓሉን ያደምቁታል።

የበዓሉ መምጣት የእነሱም ደስታ እንደሆነ ይገልፃሉ። ይህን በዓል ልዩ የሚያደርገው የተጣሉ ሰዎች ሳይታረቁ በዓሉን በፍፁም አለማክበራቸው ነው። ይህ በዓል እርቅ የሚወርድበት ትልቅ በዓል ነው። እንኳን ባላንጣዎቹ "እንስሳትና እባብም አብረው ያድራሉ ይባላል።"

በጎፋ በዓመት አንዴ የደመራ ችቦ ከተለኮሰ በኋላ ሀዘን የለም ይባላል። የበዓሉ እለት ለሞተ ሰው እንኳን አይለቀስም። ከደመራ በኋላ የማስረሻ ጭፈራ እየተጨፈረ ለቀስተኛ በር ላይ ይዞራል። ሟቹ በበዓሉ እለት ተወስዷል ይባላል። ለቀስተኞችም ለቅሶውን አቁመው "መስቃላ ዮ" እያሉ በዓሉን ማክበር ይቀጥላሉ። ይሄ ስርዓት ሀዘናቸውን እንደሚቀንስ የማህበረሰቡ ተወላጆች ይመሰክራሉ።

በጎፋ ብሔረሰብ ለዚህ በዓል ለምግብና ለመጠጥ አዘገጃጀት የሚሰጠው ትኩረት ከሌሎቹ በዓላት ለየት ያለ ነው። ለደመራ ተብሎ የሚወጣው ወጪ ለነገ የማይባል፣ ያለውም የሌለውም ሳይሳሳ የሚያወጣበት ነው። ከዋና በዓሉ በፊት የሚገኘው የደመራ ስነ-ስርዓት ትልቅ መልእክት ያዘለ ነው። ከሳምንት በፊት ከቤተሰቡ አባት ወይም ታላቅ ልጅ ችቦ የሚሆኑ የደረቁ ቀጥ ያሉ የችቦ ጭራሮዎችን ያዘጋጃል። ቀጥ ያሉ መሆናቸው ተምሳሌትነቱ ዘመኑ መልካም እንዲሆን፣ ከበሽታና መቅሰፍት እንዲጠበቁ፣ ልጆችም በአስተሳሰብና በአመለካከት ቀና እንዲሆኑ የማህበረሰቡ መልካም ምኞት ነው። የሚጠቀሙትን የእንጨት አይነት ሶልዜ ይሉታል። ዋናው ትልቁ የደመራ እንጨት እርጥብ መሆን አለበት። ይህም ዘመኑ የጥጋብና የሰላም እንዲሆን ያላቸውን መልካም ምኞት የሚገለፅበት ነው። በደመራው እንጨት ጫፍ ላይ የሚታሰረው አደይ አበባ ደግሞ

ተስፋ፣ ውበት፣ ዘር መኖሩንና የተጀመረው ስነ-ስርዓት ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍ ስለመሆኑ መልዕክት የሚተላለፍበት ነው፡፡

የችቦ አስተሳሰሩ አንደ ቤተሰቡ ቁጥርና እድሜ ይወሰናል፡፡ ይህም በአመለካከታቸው መደማመጥና መከባበር እንዲሰፍን ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ የደመራ ስነ-ስርዓት ላይ ሴቶች አይሳተፉም፡፡ በደመራው እለት ገንፎ ለማዘጋጀት ጉድ ጉድ ይላሉ፡፡ ገንፎው ከወተት፣ ከተነጠረ ቅቤ፣ ከአይብና ከበቆሎ ዱቄት የሚዘጋጅ ነው፡፡ ይህ ገንፎ ከተዘጋጀ በኋላ በአንድነት በመሰብሰብ እጃቸውን ወደ መሶቡ የሚሰዱበት ስርዓት ከምንም በላይ ፈጣሪያቸውን የሚያስቡበትና የሚማጸኑበት ነው፡፡ በሰፊ ማዕድ የቀረበውን ገንፎ “መስቃላ ዮ” እያሉ በጋራ ይቋደሱታል፡፡ የገንፎው ስነ-ስርዓት ከደመራው ቀጥሎ የሚከናወን ነው፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከቀረበው ምንባብ ምን ተረዳችሁ? በቀጣዩ ክፍልስ ምን የሚነሳ ይመስላችኋል?

የችቦ አለኳኮስ ስርዓቱ ለየት ያለ ነው፡፡ ይሄውም በመጀመሪያ ቀኑ ደንገዝገዝ ወይም ለዓይን ያዝ ሲል አባወራው በልጆቹ ቁጥር ልክ የተከኮሰውን ችቦ በመያዝ ምሰሶ ካለበት ጎጆ ቤት ውስጥ በመግባት ለገንፎ ከተጣደው ድስት ስር ከሚነደው እሳት ሁሉንም ችቦዎች ይለኩሳል፡፡ ችቦዎቹን ከለኮሰ በኋላ በቀኝ በኩል በመታጠፍ ምሰሶውን በመዞር የከብቶች በረት እንዲሁም በቀኝና በግራ የቆሙትን ግርግዳዎች “መስቃላ ዮ” እያለ በተለኮሰው እሳት እየነካካ ወደ ደጅ ይወጣል፡፡

አባት “ማስቃላ ዮ” አያለ ችቦውን በእድሜ ደረጃቸው ካካፈለ በኋላ መሃል ላይ በመሆን በወንዶች ታጅበው ደመራውን ይዞራሉ፡፡ አባት በመጀመሪያ ችቦውን ካስቀመጠ በኋላ ቀጥሎ ልጆች በእድሜያቸው ቅድመ ተከታል ያስቀምጣሉ፡፡ በዚህም ጊዜ የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ ፥ ይጨፍራሉ፡፡ ችቦ ሲታሰርና ደመራው

ሲተከል ከወንድ ልጆች መካከል በዕለቱ መገኘት ያልቻለ ቢኖር የለም ተብሎ ደመራው ሳይወጣለት አይቀርም ለሌሎች የሚደረገው ሁሉ ለእርሱም ይደረግለታል፡፡

ደመራው ከተለኮሰ በኋላ "መስቃላ ዮ" እያሉ ወደ ቤት ተመልሰው በእናቶቻቸው፣ ከእህቶቻቸውና ከባለቤቶቻቸው ጋር "መሰቃላ ዮ" ከተባባሉ በኋላ እንደገና ችቧቸውን በመያዝ በባህላዊ መሪው ተመርቀው ወደየቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ ባህላዊ መሪው የሀገሩ ባላባት "ቢታቢታንቱ" ይባላሉ፡፡ ቢታ ቢታንቱ ማለት በአካባቢው ባላባት የዚያ ቀበሌ የመሬት አስተዳዳሪና ባህላዊ መሪ እንዲሆን የተሾመ ሰው ማለት ነው፡፡ የአነጋገስ ስርዓቱም እስኪሞት የሚዘልቅ ነው፡፡ እሱ ሲሞት ልጁ ወይም ታላቅ ወንድሙ ይነግሳል፡፡

ከአያት ቅድመ አያቶች ሲወርድ ሲወራረድ የመጣው ይህ ስርዓት በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት አለው፡፡ ንግስናውን የሚሰጡት "ምራና" የሚባሉ አንጋሾች ሲሆኑ ንጉሱ ሲሞት በጊዜያዊነት በተዘጋጀ ዳስ ውስጥ የንግስና ስርዓቱን ይፈጽማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ቦርዴ የሚባል ባህላዊ መጠጥ ይጠጣል፡፡ ላምና ጥጃም በስጦታ መልክ ይሰጣል፡፡

ይህ ንግስና ከደመራ በዓል ጋርም ተያያዥነት አለው፡፡ የደመራ በዓል ሲመጣ የተጣላና የተኳረፈ የተጋደለም ይቅር ይባባላል፡፡ ይህም የሚሆነው አዲስ ዓመት ከመሆኑም በተጨማሪ በማህበረሰቡ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ቢታ ቢታንቱዎች የተጣሉ እንዲታረቁ ስለሚያስገድዱ ነው፡፡ ቢታቢታንቱዎች ለማስታረቅ መክረው አሻፈረኝ የሚል ሰው በዚያው ዓመት ውስጥ ይሞታል የሚል እምነትም አለ፡፡

የእድሜ ልክ ንግስና የሚሰጣቸው ቢታ ቢታንቱ አናታቸው ላይ ኮለቻ የሚባል ዘውድ ይደፋሉ፡፡ ከደመራ ስነ-ስርዓቱ ጎን ለጎን እርዱ ይካሄዳል ፡፡ እርዱ የሚከናወነው በአንድ ትልቅ ሰው ደጃፍ ላይ ነው፡፡ በእርዱ ስነ-ስርዓት የእንሰት ቅጠል እንደ ሽራ

ይነጠፋል፡፡ ይሄም የሚደረገው ዓመቱ እርጥብ እንዲሆን በመመኘት ነው፡፡ የእንሰት ጉዝጓዝ ላይም ስጋው ተመድቦ የዓመት ሰው ይበለን ብለው በመመራረቅ ስነ-ስርዓቱን ፈጽመው ይወጣሉ፡፡

ምንጭ፡- (ሪፖርተር ጋዜጣ፣ መስከረም 18 ቀን ፣ቅጽ 25 ቁጥር 2026፣2012 ዓ.ም

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- ለቀረቡት ፊሊጦች ተገቢውን ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (እንደ አስፈላጊነቱ)
- የፈሊጣዊ ንግግርን ፍቺ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡-

ተግባር ሁለት፡-

“ጎፋ መስቃላ ዮ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ፡፡

1. እርቅ
2. ቢታ ቢታንቱ
3. ምራና እና ዳስ
4. ቦርዴ
5. ሶልዜ
6. ከለቻ

ተግባር ሶስት፡-

ከታች በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. አጋጣሚ
2. በርካታ
3. ብዙ አይነት
4. ወሰን
5. ሊቆም
6. የሀሳብ
7. የሌለው
8. ብዙ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር


የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎቹ በቡድን በመሆን ስለማህበራዊ ግንኙነት ምንነትና ጠቀሜታ በቡድን እንዲወያዩ ያግዟቸው፤ የደረሱበትንም የጋራ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

ምዘና፡-

- የውይይት መመሪያን መሰረት አድርገው መወያየታቸውን ያረጋግጡ



## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ

ቅድመ ንባብ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ወደ ማንበብ ሂደት ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ የተማሪዎችንም ምላሽ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ጥያቄዎቹን ያንብቡላቸው፤ስለ ስዕሉም ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

የንባብ ጊዜ

ተግባር

- ✓ ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ያሉትን አንቀፆች ተማሪዎች በለሆሳስ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ከምንባቡ ለወጡት ፈሊጣዊ ንግግሮች ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲያነቡ ይዘዟቸው፤ ይከታተሏቸው፡፡

አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ተማሪዎቹ ንባባቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመሄድ ተግባር አንድ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ተማሪዎቹ ጥንድ ጥንድ ሆነው ከምንባቡ ለወጡ ፈሊጣዊ ንግግሮች ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ግበረ መልስም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሶስት

- ✓ በተግባር ሁለት ፍቺ በሰጡባቸው ፈሊጣዊ ንግግሮች ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፤ እገዛም ያድርጉላቸው፡፡

ምዘና፡-

- ምንባቡን በተገቢው መንገድ ማንበባቸውን ያረጋግጡ
- ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ
- ለፈሊጣዊ ንግግሮች ፍቺ መስጠታቸውንና ዓረፍተ ነገር መመስረታቸውን ያረጋግጡ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች

ተግባር ሁለት፡-

ከምንባቡ ለወጡ ፈሊጣዊ ንግግሮች ጥንድ ጥንድ በመሆን ፍቺ ስጡ፡፡

1. በተናጥል
2. ድምፁ የሚያምር
3. ሁሉም
4. በብዛት

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ የማህበራዊ ግንኙነትን በተመለከተ የቀረበውን ምሳሌ ጽሁፍ በማንበብ ከተሰጡት ርዕሶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ባለ ሁለት አንቀፅ ጽሁፍ እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ በተግባር አንድ ላይ የፃፉትን አንቀፅ ለጓደኞቻቸው በማንበብ እርስ በርስ እርማት እንዲሰጣጡ ያድርጓቸው፡፡

ምዘና፦

- ባለ ሁለት አንቀፅ ጽሁፍ መፃፋቸውን ያረጋግጡ
- እርስ በርስ መተራረማቸውን ይመልከቱ

መርጃ መሳሪያ፦

- ስለማህበራዊ ግንኙነት የሚገልጽ ሞዴል አንቀፅ

## ክፍል አምስት፦ ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

✓ የቀረቡትን ቃላት ከተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ። ግብረ መልስም ይስጧቸው።

ተግባር ሁለት

✓ የቀረቡትን ቃላት ከተቃራኒ ፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ። ግብረ መልስም ይስጧቸው።

ምዘና፦

- ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፦

- የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፦

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ።

1. ሐ
2. ሀ
3. በ
4. ሠ
5. መ
6. ለ
7. ረ
8. ቀ
9. ሸ

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተቃራኒ ፍቾቻቸው ጋር አዛምዱ።

1. ሐ
2. ሽ
3. ለ
4. ረ
5. ሀ
6. ሰ
7. ሠ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

✓ የቀረቡትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች ወደ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር እንዲለውጡ ያድርጉ።

✓ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አገልግሎት በመለየት ሀተታዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ መጠይቃዊና አጋኗዊ በማለት እንዲመልሱ ያድርጉ፤ እርማትም ይስጧቸው።

ምዘና፡-

- ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረታቸውን ያረጋግጡ
- ዓረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎታቸው አንፃር መለየታቸውን ይመልከቱ

# ምዕራፍ ስምንት (፰)

## ሱስ

(ክፍለ ጊዜ 9)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- አዳምጠው ተመሳሳይ ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡
- ሱስ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ይገልጻሉ፡፡
- የፅሁፉን ዋና ሀሳብ በተመለከተ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
- ያዳመጡትን ሀሳብ እንደገና ያዋቅራሉ፡፡

**የትምህርት ይዘቶች**

- ተመሳሳይ ጽሑፎች
- ሀሳብን እንደገና ማስተካከል
- ምንባብና ዘገባ
- የስርዓተ ነጥብ ምልክቶች
- የቃላት አውዳዊ ፍቺ
- ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

የትምህርቱ አቀራረብ

ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር

- ✓ተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው፡፡
- ✓በቅድመ ማዳመጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፤ ምላሻቸውንም ይቀበሏቸው፡፡
- ✓የተማሪዎቹን ምላሽ በመቀበል ያለውን የእውቀት ክፍተት ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡ የመስማት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ እንዲሳተፉ እገዛ ያድርጉላቸው፤ የምንባቡን ቅጅ ይስጧቸው፡፡

የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር

✓ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ፡፡ ከዚያም የቀረበውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡ የመስማት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ እንዲያነቡ ያመቻቹላቸው፡፡

አዳምጦ መረዳት

ተግባር አንድ

✓ማዳመጡ እንዳለቀ ወደ ተግባር አንድ በመሸጋገር ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል እንዲመርጡ ያድርጉ፡፡ እገዛም ያድርጉላቸው፡፡

ተግባር ሁለት

✓ከምንባቡ ለወጡት ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡

"ትምባሆ"

በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የዓለም ጤና ድርጅት ጥናቶች እንደሚያሳዩት ትምባሆ በዓለም ላይ ሰፋ ያሉ ጉዳቶችን አስከትሏል፡፡ በዓመት አራት ሚሊዮን አካባቢ የሚሆነው ሞት በትምባሆ ምክንያት የሚከሰት ሲሆን፣ ይህም ትምባሆ ከአስር አዋቂዎች ለአንዱ ሞት ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በጥናቶቹ ትንበያ መሰረት እ.ኤ.አ በ2030 ከአጠቃላይ ሞት በትምባሆ ምክንያት የሚመጣ ሞት በፍጥነት እየጨመረ እንደሚሄድ ነው፡፡ በትምባሆ ምክንያት የሚመጣውን የሞት ቁጥርም በዓመት ወደ አስር ሚሊዮን ወይም ከስድስት ሰው አንዱ የሚሞትበት ሁኔታ እንደሚፈጥር ይታመናል፡፡ ይህ ማለት በአሁኑ ወቅት በህይወት ያሉ ወደ 500 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች በትምባሆ ምክንያት መሞታቸው አይቀርም ማለት ነው፡፡

ይህ አሃዝ (ቁጥር) በአንድ ወቅት ባደጉ አገሮች እየጨመረ የመጣ እንደሆነ መረጃዎች ቢያሳዩም በአሁኑ ወቅት ችግሩ በማደግ ላይ ባሉት ሀገሮች እጅጉን ተሰራጭቷል፡፡ እ.ኤ.አ በ2030 አሁን ካለበት ሃምሳ በመቶ በትምባሆ ምክንያት የሚከሰተው ሞት በማደግ ላይ

ባሉት ሀገሮች ሰባ በመቶ እንደሚሆን ጥናቶች ያሳያሉ። ችግሩን ይበልጥ የሚያወሳስበው ደግሞ አሁን ዓለም የገባችበት ሉላዊነት (Globalization) ዘመን መሆኑ ነው።

በዚህ ዘመን ትምባሆ ከአንዱ ሀገር ወይም አህጉር ወደ ሌላው በቀላሉ እንዲደርስ ትምባሆን የሚያስተዋውቁ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችና የመገናኛ ብዙሃን መስፋፋታቸውና የባህል ልውውጡ በቀላሉ መስፋፋት ትምባሆን በማስፋፋት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አድርጓል።

የችግሩ አሳሳቢነት የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በትምባሆ ቁጥር ላይ ተመሳሳይ አቋም እንዲይዝ ያስቻለ ሲሆን፣ ይህ አቋም ወደ ተግባራዊ ቁርጠኝነት ተቀይሮ ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፍ እንዲቀረፅ ሰበብ ሆኗል። እ.ኤ.አ በ2003 በዓለም ጤና ድርጅት አባል ሀገሮች የፀደቀ ሲሆን፣ በአሁን ወቅት አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሀገሮች ስምምነቱን ፈርመውታል። ይህ ስምምነት ትምባሆን ለመቆጣጠር የተለያዩ ዘዴዎችን የቀረፀ ሲሆን፣ አባል ሀገሮችም ላይ የተለያዩ ግዴታዎችን ይጥላል። ሀገራችን ኢትዮጵያም የካቲት 25 ቀን 2004 ዓ.ም ስምምነቱን ተቀብላ አጽድቃለች።

*ተማሪዎች እስካሁን ከተነበበው ምንባብ በመነሳት ስለትምባሆ ምን ተረዳችሁ? በቀጣዩ ክፍልስ ምን የሚነሳ ይመስላችኋል?

ሀገራችን እንደሌላው የዓለም ክፍል ሁሉ ዜጎቿ በትምባሆ ተጠቂ የሆኑባት ስለሆነች የችግሩን አሳሳቢነት በመገንዘብ የተቋም አደረጃጀት በመቅረጽ በመንቀሳቀስ ላይ ናት። ትምባሆ ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ላይ እንዳይጨስ የሚከለክል ህግ ወጥቷል።

ሲጋራ አጫሾች ከማያጨሱት ይበልጥ ለካንሰርና ለሌሎች ተመሳሳይ በሽታዎች የመጠቃታቸው እድል ሰፊ መሆኑ ተረጋግጧል።

ሲጋራ ማጨስ ለተለያዩ በሽታዎች የሚያጋልጥ እንደሆነ በሰፊው ታውቋል፡፡ በሲጋራ ውስጥ "ታር" ፣ ሞኖ ኦክሳይድና ኒኮቲን" የተሰኙ ሱስ አስያዥ ንጥረ-ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህ ንጥረ-ነገሮች አጫሾቹን ለሱስ ያጋልጣሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ሱስ በማስያዝ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ያለው "ኒኮቲን" የተባለው ንጥረ-ነገር ነው፡፡ "ኒኮቲን" በትምባሆ ቅጠል ውስጥ የሚገኝ ፈሳሽ ንጥረ ነገር ሲሆን የማነቃቃትና ሱስ የማስያዝ ሀይሉ ከፍተኛ ነው፡፡

ሲጋራ የሚያጨሱ ሰዎች በሲጋራው ምክንያት በሰውነታቸው ላይ የተለያዩ ለውጦች ይከሰታሉ፡፡ "የአድሬናልን" ዝውውር ይጨምራል፤ የምግብ ፍላጎት ይቀንሳል፤ የልብ ምት ይጨምራል፤ ሆርሞኖቹ በብዛት ይጨምራሉ፡፡ የምግብ ፍላጎት ይቀንሳል፡፡ የልብ ምት ይጨምራል፡፡ እንዲሁም የአፍ ጠረንን ይለውጣል፡፡ እንዲሁም የጥርስን ንፅህናና ጤንነት ያውካል፡፡

በተለያዩ ሀገሮች ህግ ትምባሆ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች እንዳይጨሱ የሚከለከልባቸው ምክንያቶች መካከል ዋነኛው ትምባሆ በማይጠቀሙ ሰዎች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ነው፡፡ የሚያጨሱ ሰዎች ራሳቸው ላይ ከሚያመጡት የጤና ችግር ባልተናነሰ በአካባቢው የሚገኘው የማያጨሰው ሰው ላይ የሚያመጡት አደጋ አለ፡፡ ይህን ከግንዛቤ በማስገባት ራሳችንን እና ሌሎችንም ከዚህ ጎጂ ሱስ መጠበቅ የሁላችንም ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝበን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ምንጭ፤- (ሪፖርተር ጋዜጣ፣ ቅፅ 19፣ ቁጥር 1434፣ እሁድ ጥር 18/2006 ለክፍሉ ተሸሽሎ የቀረበ)፡፡

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- ስለ ትምባሆ ጉዳት ይጠይቋቸው

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (እንደ አስፈላጊነቱ)
- የትምባሆን ጎጂነት የሚያሳዩ ምስሎች

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### ተግባር አንድ

ቀጥለው ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. ለ
2. መ
3. ሀ
4. ሐ
5. መ

### ተግባር ሁለት

በ “ሀ” ስር ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ቃላት በ “ለ” ስር ከቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

1. ሰ
2. ሀ
3. መ
4. ለ
5. ሐ
6. ሸ
7. ሠ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ተግባር**

✓ካዳመጡት ምንባብ ላይ ስለ ትምባሆ ምንነትና ጎጂነት ጠቅለል አድርገው ማብራሪያ እንዲሰጡ ያድርጉ

**ምዘና፡-**

- የምንባቡን ሀሳብ ጠቅለል አድርገው ንግግር ማድረጋቸውን ያረጋግጡ

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ቅድመ ንባብ**

**ተግባር**

✓ተማሪዎች ወደ ማንበብ ሂደት ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ የተማሪዎችንም ምላሽ ይቀበሏቸው፡፡

✓በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ጥያቄዎቹን በማንበብ እንዲዘጋጁ ያድርጉ፤ ስለ ስዕሎችም ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

**የንባብ ጊዜ**

**ተግባር**

✓ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ያሉትን አንቀፆች ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

✓የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ

✓ተማሪዎቹ ንባባቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመሄድ ተግባር አንድ ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት በጽሑፍ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

✓ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡

ተግባር ሶስት

✓ወደ ሱስ የሚያስገቡ ምክንያቶችንና የሚያስከትሉትን ጉዳት በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

✓ከውይይት በኋላ የደረሱበትን ድምዳሜ በተወካያቸው አማካኝነት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ እገዛም ያድርጉላቸው፡፡

ምዘና፡-

- ምንባቡን በተገቢው መንገድ ማንበባቸውን ይከታተሉ
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠታቸውን ያረጋግጡ
- ውይይት ማድረጋቸውንና በተወካያቸው አማካኝነት መከታተላቸውን ያረጋግጡ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ ሀሳብ ከያዙ እውነት ትክክለኛ ሀሳብ ካልያዙ ሀሰት በማለት መልሱ ::ለመልሳችሁ ምክንያት ስጡ::

1. ሀሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. ሀሰት
6. እውነት

ተግባር ሁለት

ከታች ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ አዳዲስ ቃላት እና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ::

1. የመጀመሪያ
2. ታንያ
3. መምጣት
4. አሰቡ (አቀዱ)
5. ሄደ
6. ይገፋፉሉ
7. አድራሻው
8. ጠፋ
9. ያቅታቸዋል
10. ብሶ ( ተበላሽቶ)

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታወሻ

### ስርዓተ ነጥቦች

በወረቀት ላይ የሰፈረ ሀሳብ መልዕክቱ ግልፅ ሆኖ እንዲተላለፍ ስርዓተ ነጥቦች የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ በፅሁፉ ላይ ነጥቦችን አስተካክሎ ካለመጠቀም የተነሳ ዓረፍተ ነገሮች ያሻማሉ፤ መልእክቶች ይዛባሉ፤ ሃሳቦች ይድበሰበሳሉ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ በርካታ ስርዓተ ነጥቦች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን እንመልከት፡፡

1. አንድ ነጥብ (·) ፡- አንድ ነጥብ ይዘት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በሶስት የተለያየ መልክ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ እነሱም፡-
   - ቃላትን በምህፃረ ቃል አሳጥሮ ለመፃፍ ያገለግላል፡፡

     ምሳሌ፡- ተ.መ.ድ      የተባበሩት መንግስታት ድርጅት
   - ብርና ሳንቲሞችን እንዲሁም ሙሉና ክፍልፋይ ቁጥሮችን ለመለየት

     ምሳሌ፡- 6.50      (ስድስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም)
   - መለያ ቁጥሮችን ወይም ሆሄያትን ከዋናው ሀሳብ ለመለየት

     ምሳሌ፡- 1.እናት አባትን ማክበር
2. ሁለት ነጥብ (፡) ፡- ሁለት ነጥብ ከታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡
   - በቃላት መካከል በመግባት አንዱን ቃል ከሌላው ለመለየት ያገለግላል፡፡

     ምሳሌ፡- ቶሎሳ፡ምሳውን፡በላ፡፡
   - ሰዓትና ደቂቃን ለመለየት ያገለጋል፡፡

     ምሳሌ፡- 2:30 (ሁለት ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ)

3. ሁለት ነጥብ ከሰረዝ (፡-) ፡- ሁለት ነጥብ ከሰረዝ ቀጥለው የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡

- ይህ ስርዓተ ነጥብ መሪ ሃሳቡን ተከትለው ወደሚመጡ ዝርዝር ነገሮች ለማንደርደር ያገለግላል፡፡

  ምሳሌ፡- ቋንቋ አራት ክሂሎች አሉት፡፡ እነሱም፡- ማንበብ፣ መፃፍ፣ መናገርና ማዳመጥ ናቸው፡፡

- ምሳሌ ለመጥቀስ ያገለግላል፡፡

  ኢትዮጵያ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ናት፡፡ ምሳሌ፡-

4. ነጠላ ሰረዝ (፣ ፥) ፡- ሁለት አይነት ነጠላ ሰረዞች አሉ፡፡ አገልግሎታቸውም፡-

- የመጀመሪያው ተመሳሳይ ሙያ ያላቸውን ተከታታይ ቃላት ለመለየት

  ምሳሌ፡- ድርጅታችን ጨው፣ ስኳር፣ ዘይት ወዘተ. ያከፋፍላል፡፡

- ሁለተኛው ደግሞ ምዕራፍና ቁጥርን ለመለየት ያገለግላል፡፡

  ምሳሌ፡- ማቴ. 24፥15

5. ድርብ ሰረዝ (፤) ፡- ድርብ ሰረዝ አቻ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን ለማያያዝ ያገለግላል፡፡

   ምሳሌ፡- በጧት ተነሳ፤ ልብሱን ለበሰ፤ ቁርሱን በላ፤ ደብተሩን ይዞ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

6. ሶስት ነጥብ (...)፡- ነጠብጣብ ተብሎ ይጠራል፡፡ አገልግሎቱም፡፡

- ከተወሰዱ ሃሳቦች ውስጥ ተቆርጠው የቀሩ፣ መሀል ላይ የተዘለሉ ወይም ያላለቁ ሀሳቦች መኖራቸውን ለማመልከት

  ምሳሌ፡- ... ሰባት ሰዓት ሙሉ አስቀምጦኝ ጠፋ፡፡ ... ብጠብቅም ሊመጣ አልቻለም፡፡ እኔም...

- የትንፋሽ መቆራረጥንና የሀሳብ አለመያያዝን ለማመልከት

  ምሳሌ፡- የተደረገ...ልኝን...በቃላት መግ...ለፅ...አልች...ልም፡፡

- ተመሳሳይ ነገሮች የሚቀጥሉ መሆናቸውን ለማመልከት

ምሳሌ፡- ሙሉቀን እንደ ወንበር፣ አልጋ፣ ጠረጴዛ... የመሳሰሉትን ብዙ ብር አውጥቶ ገዛ፡፡

7. ትእምርተ-ጥቅስ ፡- ሁለት አይነት ትእምርተ-ጥቅሶች አሉ፡፡ እነሱም፡-

ሀ. ድርብ ትእምርተ-ጥቅስ (“ ”) ፡-

- የሌላ ሰው ሀሳብ በፅሁፋችን ስንጠቀም ሀሳቡ የኛ አለመሆኑን ለማመልከት ያገለግላል፡፡

ለምሳሌ፡- “ከመሞት መሰንበት” በማለት ተናገሩ፡፡

- አንዳንድ የተውሶ ቃላት በቋንቋው ውስጥ ሲፃፉ ባእድነታቸውን ለማሳየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- የእግሩ ህመም መንስኤ የ “ነርቭ” መሸማቀቅ ነው፡፡

- ጸሀፊው በትርጉማቸው የማያምንባቸው አባባሎች ለመለየት ይገለገልባቸዋል፡፡

ምሳሌ፡- እኔን አልሰማ ካልከኝ አከክስትህ እንደመከረችህ “የጨዋ ልጅ” ፈልገህ አግባ፡፡

- የሁለት ሰዎችን ምልልሳዊ ንግግር ለየብቻ በደንብ ለማሳየት ይረዳል፡፡

ለምሳሌ፡- “ዛሬ ት/ቤት ሄደሃል?”

“አዎና! ግን ለምን ጠየቅከኝ?”

“የትራንስፖርት ችግር ስለነበረ ነዋ!”

ለ. ነጠላ ትእምርተ-ጥቅስ (‹ ›) ፡- ይህ ምልክት ጸሀፊው በጠቀሰው ጥቅስ ውስጥ ሌላ ጥቅስ (የሶስተኛ ሰው ሀሳብ) ካጋጠመው ለብቻው ለማቅረብ የሚጠቅም ምልክት ነው፡፡

ምሳሌ፡- “በርትተን ለመማርና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ‹ሁልጊዜ ትጉ› የሚለውን የመምህራችንን ምክር እናስታውስ” በማለት የክፍል አለቃዋ ጓደኞቿን መከረች፡፡

8. ትምህርተ-አንክሮ(!) ፡- ቃለ አጋኖ በመባልም ይጠራል፡ ፡ መገረምን፣ መደነቅን፣ ንዴትን፣ ትእዛዝን፣ ማሞካሸትን፣ ማድነቅን፣ ቁጣን፣ ጩኸትንና ለቅሶን የመሳሰሉትን ለማመልከት ያገለግላል።

ምሳሌ፡- ዛሬ መሄድ አለብህ! (ትእዛዝን ለመግለፅ)

ጎሽ! አንጀቴን አራስከው (ማሞካሸትና ማድነቅን ለመግለጽ)

ኤጭ! ወዲያ ሂድልኝ (ቁጣን ለመግለፅ)

9. ትእምርተ-ስላቅ (¡)፡- ምፀትን፣ ቀልድና ተሳልቆን ያመለክታል።

ምሳሌ፡- አቤት ውፍረት¡ በር አያስገባትም እኮ (በጣም ቀጭን የሆነችን ልጅ)

10.ትእምርተ-ጥያቄ(?)፡- የጥያቄ ምልክት በመባልም ይታወቃል። ጥያቄያዊ ጽሑፎችን ለመፃፍ ያገለግላል። በተጨማሪም የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ሲፅፍ ቀንና ቁጥርን ለመፃፍ ያገለግላል።

ምሳሌ፡- የቤት ስራህን ሰርተሃል ?

11. እዝባር (/)፡- አቆልቋይ በመባል ይታወቃል። እንደ ይዘት ሁሉ ምህፃረ ቃላትን ለመፃፍ ያገለግላል።

ምሳሌ፡- ወ/ሮ - ወይዘሮ፣ ጽ/ቤት - ጽህፈት ቤት

12. ቅንፍ ( )፡- ወይም የሚለውንም አማራጭ ቃል ተክቶ ይገባል

ምሳሌ፡- ነገ ጠዋት ወላጅህን (አሳዳጊህን) ይዘህ እንድትመጣ።

13. ሰረዝ(-)፡- ጭረት በመባል ይታወቃለል። ሁለት አይነት ሰረዞች አሉ። እነሱም፡-

ሀ. ንዑስ ሰረዝ (-)፡-

- ጥምር ቃላትን ለማመልከት ያገለግላል።

  ምሳሌ፡- ቃለ-ጉባኤ

- ዝርዝር ነጥቦችን ለየብቻ ለማሳየት ያገለግላል።

ለ. አብይ ሰረዝ (–)፡- እስከ የሚለውን ቃል ለማመልከት ያገለግላል። ምሳሌ፡- ከአዲስ አበባ – ባህር ዳር

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

✓ስለ ስርዓተ ነጥብ ምንነትና አገልግሎት ማስታወሻውን እንዲወስዱ ያድርጉ፤ ማብራሪያም ይስጧቸው፡፡

✓በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው እንዲያስገቡ ያድርጉ፤ ድጋፍም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሁለት

✓በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ እንዲያስገቡ ያድርጉ፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- በዓረፍተ ነገሮችና በአንቀጽ ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥቦች መጠቀማቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የስርዓተ ነጥብ አይነቶችን ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ከታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ አስገቡ፡፡

1. በአዋሽ ፓርክ ውስጥ አንበሳ፣ ቀበሮ፣ ጅብ፣ ሚዳቋ፣ ዝንጀሮ እና ጦጣ የመሳሰሉት እንስሳት ይገኛሉ፡፡
2. በርቀት እንደተቀመጠ አያት፤ እሷም አይታው ነበር፡፡
3. ወደዚህ ስፍራ ከዚህ ቀደም መጥቶ አያውቅም፡፡
4. “ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው” በማለት ቢኒያም

በለጠ ተናገረ፡፡

5. የትምህርት ቤቱን ስርዓት ማክበር የሁሉም ተማሪ ግዴታ ነው!
6. ጎሽ የኔ አንበሳ ከመቶው ሰላሳ አመጣህ¡
7. ተመድ የወባ በሽታ ወረርሽኝን ለመቀነስ ጠንክሮ እየሰራ ነው፡፡
8. ሀገርን የማልማት ኃላፊነት የማን ነው?
9. የቀለም አባቴ (መምህሬ) ጎበዝ እንድሆን መከረኝ፡፡
10. ኢትዮጵያ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ናት፡፡ እነሱም፡- አባይ፣ ባሮ፣ ተከዜ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ወዘተ. ናቸው፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ተግባር

✓በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ተዘውታሪ ቃላት ከታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው እንዲያስገቡ ያድርጉ፡፡

ምዘና፡-

- የቀረቡትን ተዘውታሪ ቃላት በተገቢ ቦታቸው ማስገባታቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- ተዘውታሪ ቃላትን የያዘ ቻርት

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር፡-

በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ተዘውታሪ ቃላት ከታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛው ቦታቸው አስገቡ፡፡

1. ብልሀቶችን
2. በለጋ
3. የውዴታ ግዴታ
4. ለስቃይ
5. በጽኑ
6. ልማዳዊ
7. ክፍፍል

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

✓በቀረበው ምሳሌ መሰረት ውስብስብ ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፤ እርማትም ይስጡ፡፡

ምዘና፡-

- ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መፃፋቸውን ያረጋግጡ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ (፱)

## የሀገር ፍቅር

(ክፍለ ጊዜ 12)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማ:- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- አዳምጠው የጽሑፉን ፅንሰ ሀሳብ ከህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- የሀገር ፍቅርን ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- ለተወሰነ ዓላማ ያነባሉ፡፡
- የሀገር ፍቅርን ያደንቃሉ፡፡
- ምስሎችን ይገልፃሉ፡፡

**የትምህርት ይዘቶች**

- ያዳመጡትን ጽሁፍ ከህይወታቸው ጋር ማዛመድ
- በአውድ ውስጥ መግባባት
- ለተወሰነ ዓላማ ማንበብ
- ገላጭ ጽሁፍ
- አውዳዊ ፍቺ
- ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ማዳመጥ

#### ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው።
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው።
- ✓ በቅድመ ማዳመጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፤ ምላሻቸውንም ይቀበሏቸው።
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ስለምስሉ ማብራሪያ ይስጧቸው።
- ✓ ከየቡድኖቹ በውይይት የደረሱበትን መደምደሚያ በመቀበል ያለውን የእውቀት ክፍተት ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው።
- ✓ የመስማት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ የሚነበበውን ፅሁፍ በግላቸው እንዲያነቡ ያመቻቹላቸው።

### የማዳመጥ ጊዜ

#### ተግባር

- ✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ እየመዘገቡ እንዲያዳምጡ ያድርጉ።
- ✓ የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው።
- ✓ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ። ከዚያም የቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው።

አዳምጦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ማዳመጡ እንዳለቀ ወደ ተግባር አንድ በመሸጋገር ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በያዙት ሀሳብ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት በጽሑፍ እንዲመልሱ ያድርጉ፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው።

ተግባር ሁለት

- ✓ በቀረበው ሳጥን ውስጥ ያሉትን ቃላትና ሀረጋት በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛ አውዳቸው እንዲያስገቡ ያድርጉ።

## "የአድዋ ድልና የሀገር ፍቅር ስሜት"

የአድዋ ድል ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ ሀገራችን ነፃነቷን አስከብራ የቀጠለችበት፤ኢትዮጵያዊያን በሉዓላዊነት ጉዳይ ያለን አንድነትና ቁርጠኛ አቋም የታየበት፤ ቅኝ ገዥ አውሮፓዊያን ፈፅሞ ባልተጠበቀ ሁኔታ በጥቁር አፍሪካዊያን አሳፋሪ ሽንፈት የተከናነቡበት እና በአፍሪካዊያን ብሎም በዓለም ታሪክ ከፍ ያለ ታላቅ ድል ነው።

ለአድዋ ጦርነት ትክክለኛ ምክንያት በወቅቱ አውሮፓዊያን አፍሪካን ለመቀራመት የነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎትና ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ የነበራት ጉጉት ነው። ጣሊያን ኢትዮጵያን በቁጥጥሯ ስር ለማድረግ በቀጥታ ጦርነት ውስጥ ከመግባት ይልቅ የተንኮል ቃል ያለበት የውል ስምምነት ማድረግን መረጠች።

በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ለተፈጠረው አለመግባባት ዋና

ምክንያት የሆነው ሃያ አንቀፆችን የያዘው የውጫሌ ውል ስምምነት ሚያዝያ 25 1881 ዓ.ም ተደርጓል፡፡ የውጫሌ ውል የሚለው ስያሜ የተሰጠው አፄ ዮሃንስ 4ኛ እንደሞቱ አፄ ምኒልክና የጣሊያን መንግስት ተወካይ ኮንት ፔትሮ አንቶሎኒ ይገኙበት በነበረው ቦሩ ሜዳ አካባቢ ውጫሌ ተብሎ በሚጠራው ቦታ የተደረገ ስለሆነ ነው፡፡

የውጫሌ ውል ስምምነት በአማርኛና በጣሊያንኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ ሲሆን በአንቀፅ 17 የተካተተው ድንጋጌ መሰረታዊ የሚባል የትርጉም ልዩነት ነበረው፡፡አፄ ምኒልክ በአንቀፅ 17 የጣሊያንኛ ቋንቋ የተፃፈውን የኢትዮጵያዊያን ሉዓላዊነት ለጣሊያን የሚሰጥ የተንኮል ቃል ያለበት መሆኑን የተረዱት በሃምሌ ወር 1881 ዓ.ም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ሁለቱ ሀገራት የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ ስላልቻሉ የአድዋ ጦርነት የማይቀር ጉዳይ ሆነ፡፡

በመጨረሻም ጣሊያን ኢትዮጵያን አባብላ በቁጥጥር ስር ለማዋል ያደረገችው ሙከራ አለመሳካቱ በሁለቱ ሃገራት መካከል ያለው አለመግባባት እንዲቀጥል አድርጓል፡፡ ይህም ኢትዮጵያዊያን አኩሪ ድል ያስመዘገቡበትና ጣሊያን አሳፋሪ ሽንፈት የተከናነበችበት ጦርነት እንዲካሄድ ግድ ሆኗል፡፡ አጼ ምኒልክ <<ክተት ሰራዊት ምታ ነጋሪት>> ብለው አዋጅ ካስነገሩ በኋላ ከመናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ 1066 ኪ.ሜ ርቀት ተጉዘው አድዋ ገቡ፡፡

ጦርነቱም የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ተጀመረ፡፡ ከእልህ አስጨራሽ ውጊያ በኋላ ረጅም ርቀት በእግራቸው ጋራ ሸንተረሩን አቋርጠው ወደ አድዋ የተመሙት ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተንቀሳቀሱ የገበሬ ሰራዊት በወታደራዊ አካዳሚ የሰለጠነውን የአውሮፓ ወራሪ የጣሊያን ጦር በታላቅ ጀብዱ ማሸነፋቸው ተረጋገጠ፡፡በዚያ ወቅት ከተገጠሙ ስነ-ቃሎች መካከል እነዚህ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣
ግብሩ እንቁላል ነበር ይሄን ጊዜ አበሻ፡፡
ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ ፣
መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ ፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከተነበበው ምንባብ ስለአድዋ ምን ቁም ነገር አገኛችሁ? በቀጣዩ ክፍልስ ምን የሚነሳ ይመስላችኋል?

ስለ አድዋ ሲነሳ አብሮ ስማቸው የሚነሳው እቴጌ ጣይቱ ብጡል ናቸው፡፡ እቴጌ ጣይቱ ከጦርነቱ በፊትም በአደራዳሪነት፣ ከጦርነቱ በኋላም በአዋጊነት ትልቅ ሚና ነበራቸው፡፡ ድርድሩን እስከ መጨረሻ ታግሰው በስተመጨረሻ ግን ውርድ ከራሴ በማለት ጦር በመምራት ጭምር የተሳተፉ ታላቅ ገድል የፈፀሙ ጀግና መሪ ናቸው ፡፡

የአድዋ ድል ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው በሰባተኛ ዓመቱ በ1895 ዓ.ም ነበር፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በየዓመቱ በደማቅ ሁኔታ እየተከበረ ይገኛል፡፡ ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን ሀገራቸውን ከጠላት ለመከላከል እንደከፈሉት መስዋዕትነት እኛ የአሁን ሃገር ተረካቢዎች ሀገራችን በምትፈልገው የስራ መስክ የተጣለብንን ሃላፊነት በተገቢው መንገድ መወጣት አለብን፡፡ ሀገር ማደግ የምትችለው በተዓምር ሳይሆን ልጆቿ በሁሉም አቅጣጫ ሲተባበሩና ቅድሚያ ሲሰጧት ነው፡፡በሃገር ፍቅር ስሜት ለሃገራቸውና ለወገናቸው የሚቆጩ ዜጎችን ጉልበትና እውቀት፣ ልምድና ሃብት ከጫፍ ጫፍ በመተባበር በድህነት፣ በመሀይምነት፣ በበሽታ፣ በሙስናና በሌሎች ችግሮች ላይ የጋራ ክንዳቸውን እንዲዘረጉ የማድረግ ሃገራዊ ተቋም በመፍጠር ይገነባል፡፡

በሃገር ውስጥ ለተፈጠረ ችግር በጋራና በመተባበር ሀገሪቱን ከችግር ማውጣት እንጂ፤ ችግር አለ ተብሎ ከሃገር መሸሽ ተገቢ አይደለም፡፡ ሁሉም በግልና በጋራ ለሃገር አርበኛ የመሆን ግዴታ አለበት፡፡ አርበኛ በማናቸውም ረገድ ለሀገሩ የሚያስፈልግ ተግባር የሚፈፅም እንጂ

የሚያሳፍር ተግባር የሚሰራ አይደለም ።

ምንጭ:- (ጠና ደዎ፣ ሰው፣ ግብረገብና ስነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 2008 ዓ.ም እና ኢካሽ 25ኛ ዙር የጋዜጠኝነት ሰልጣኞች መጽሄት፣ የካቲት 2013 ዓ.ም፣ ኖቫ ማተሚያ ቤት) ።

ምዘና:-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- ስለ ሀገር ፍቅር ምንነትና መገለጫዎች ማብራራታቸውን ያረጋግጡ
- ቃላትን በትክክለኛ አውዳቸው መጠቀማቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ:-

- መቅረፀ ድምፅ (አስፈላጊ ከሆነ)
- የአድዋ ጦርነትን የሚያሳዩ ምስሎች

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ:-

ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በጽሑፍ መልሱ።

| | |
|---|---|
| 1. ሀሰት | 4. እውነት |
| 2. ሀሰት | 5. ሀሰት |
| 3. እውነት | 6. እውነት |

ተግባር ሁለት፡-

ከታች በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት ቀጥለው በቀረቡት ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛ አውዳቸው ውስጥ አስገቡ፡፡

1. ሉዓላዊነት
2. ገድል
3. መና
4. ለመቀራመት
5. አርነታቸውን
6. የጋራ ክንዳቸውን
7. የአይበገሬነት
8. መናገሻ
9. የተከናነበበት

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

የትምህርቱ አቀራረብ


ተግባር

- ✓ ስለውይይት መመሪያ ገለጻ ይስጧቸው፡፡ የሀገር ፍቅር ለምን ያስፈልጋል? ምንስ ጥቅም አለው? እንዲሁም በአሁኑ ሰዓት ለሀገራችሁ ምን አስተዋፅኦ እያደረጋችሁ ትገኛላችሁ? ወደ ፊትስ ምን ለማድረግ አስባችኋል? በሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

- ✓ ተወያይተው የደረሱበትን የጋራ ሀሳብ በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ እገዛም ያድርጉላቸው፡፡

ምዘና፡-

- መመሪያውን ተከትለው ውይይት ማድረጋቸውን ያረጋግጡ



# ክፍል ሶስት፡- ንባብ

## የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ንባብ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ወደ ማንበብ ሂደት ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ የተማሪዎችንም ምላሽ ይቀበሏቸው፤የቀረበውን ስዕል ገለፃ ያድርጉላቸው።
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ጥያቄዎቹን ያንብቡላቸው።

### የማንበብ ሂደት

ተግባር

- ✓ ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ያሉትን አንቀፆች ተማሪዎች ተራ በተራ እየተነሱ እንዲያነቡ ያድርጉ፤
- ✓ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲያነቡ ይዘዟቸው፤ ይከታተሏቸው።

### አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ተማሪዎቹ ንባባቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመሄድ ተግባር አንድ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ።

ተግባር ሁለት

✓ ተግባር ሁለት ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሶስት

✓ ስለንባብ ምንነት፣ ዓላማና አይነቶች በመምህሩ መምሪያ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ ይስጧቸው፤ ገለፃም ያድርጉላቸው፡፡

✓ ተግባር ሶስት ላይ ባለው ትዕዛዝ መሰረት በቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ያለውን መረጃ በመጠቀም ከታች የቀረበውን ሰንጠረዥ እንዲያሟሉ ያድርጓቸው፡፡

## ማስታወሻ

### የንባብ ስልቶች (ዘዴዎች)

"ንባብ" አንድን ጽሑፍ አንብበን መልእክቱን የምንረዳበት የክሂል ዘርፍ ነው፡፡ የንባብ ዘዴዎች አራት ናቸው፡፡ እነሱም፡- የአሰሳ ንባብ፣ ሰፊ ንባብ፣ ጥልቅ ንባብና የገረፍታ ንባብ ናቸው፡፡

1. አሰሳ ንባብ፡- ከአንድ ምንባብ ውስጥ ቁንጽል መረጃ ለማውጣት የምንጠቀምበት የንባብ አይነት ነው፡፡

   ምሳሌ፡- ከአንድ ሰው የሕይወት ታሪክ ውስጥ የተወለደበትን ቦታ ወይም ዓመተ ምህርት ለማግኘት የምንጠቀምበት የንባብ ስልት ነው፡፡

2. ሰፊ ንባብ፡- ይህ የንባብ አይነት የምንባቡን ሙሉ መረጃዎች በማንበብ ተከታታይ የድርጊት ክንውኖችን እና ትምህርት ሰጭና አዝናኝ ፅሁፎችን ለማንበብ የሚረዳ ስልት ነው፡፡

   ምሳሌ፡- ልቦለድ

3. ጥልቅ ንባብ (ምርምራዊ ንባብ) ፡- ስለአንድ ጉዳይ የሚያስረዳ የአፃፃፍ ስርዓት ጀምረን አንድ በአንድ ተንትነን እና ነጥለን የምናነብበት የምንገመግምበት ስልት ነው፡፡

   ምሳሌ፡- ለፈተና ስንዘጋጅ የምናነብበት መንገድ ነው፡፡

4. የገረፍታ ንባብ፡- ይህ የንባብ ስልት የቀረበው ፅሁፍ ስለምን እንደሆነ ጥቅል መረጃ የማግኛ መንገድ ነው፡፡ በአጭር ጊዜ በርካታ ቃላትን የመመልከት ልምድን ይጠይቃል፡፡

ምሳሌ፡- አንድን ፅሁፍ የያዘውን መረጃ ጠቅለል አድርገን የምንገነዘብበት ነው፡፡

ከላይ ከቀረቡት የንባብ አይነቶች ውስጥ በየትኛው የንባብ አይነት ማንበብ እንዳለብን የሚወስነው የምናነብበት ዓላማ ነው፡፡
ሰዎች ለተለያዩ ዓላማዎች ያነባሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡-

1. ለጥንቃቄ (ራስን ከአደጋ ለመከላከል)
2. ለመደሰት (ለመዝናናት)
3. አዲስ ነገር ለመማር፣ ለማወቅና ለመገንዘብ እንዲሁም መረጃን ለማግኘት ወዘተ. የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡
   ምሳሌ፡- ቁጥር፣ ቀንና ዓመተ ምህርትን ከንባቡ ውስጥ ለማውጣት የአሰሳ ንባብ ተመራጭ ነው፡፡ለፈተና ከሆነ የምናነበውጥልቅ ንባብ ተመራጭ ነው፡፡

ምዘና፡-

- ምንባቡን በተገቢው መንገድ ማንበባቸውን ይከታተሉ
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠታቸውን ያረጋግጡ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት፡-

ቀጥለው ለቀረቡት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ዘዴ
2. አስቤ
3. ሳይሰለቹ
4. ደጋፊ
5. አስተዋጽኦ
6. አስተዋይ
7. እውነት
8. ጠጋኝ
9. ማረጋገጫ
10. ማዘን

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎቹ የቀረበውን የአድዋን ጦርነት የሚያሳይ ምስል በደንብ ተወያይተው እንዲገነዘቡ ያድርጉ፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ አይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ስለምስሉ በቂ ገለፃ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ምስሉን መሰረት በማድረግ ሁለት አንቀፅ እንዲፅፉ ያድርጉ፤ ድጋፍም ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- የቀረበውን ምስል በጽሑፍ መግለጽ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ለተሰመረባቸው ያልተዘወተሩ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ ከቀረበው ግጥም ውስጥ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ድጋፍም ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- ለቀረቡት አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

### በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

ከታች በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ለተመሰረተባቸው ያልተዘወተሩ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ከጠላቶቹ
2. ከጋቢ የሚበልጥ ትልቅ ሸማ
3. ኮባ
4. ምግብ
5. ቀጫጭን እንጨት

6. መጣደፍ (መዋከብ)

7. ድንኳን (መጠለያ)

8. በነገስታት ራስ ላይ የሚደፋ የንግስና ምልክት

9. ሲመሻሽ

10. ለአጭር ጊዜ

ተግባር ሁለት፡-

ከታች የቀረበውን ግጥም በማንበብ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. መንገድ | 5. በሀይሉ |
| 2. ተሯሩጠው | 6. አዟዟረ |
| 3. ተገፋፋ | 7. ውሳኔ ስጡ |
| 4. ተደባድበው | 8. ማበጠሪያ |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

✓ ቃላቱን በቅደም ተከተላቸው አዋቅረው ውስብስብ ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- ቃላቱን በቅደም ተከተላቸው አዋቅረው ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መመስረታቸውን ያረጋግጡ

# ምዕራፍ አስር (፲)

## ቃላዊ ግጥም

(ክፍለ ጊዜ 12)

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣

- ➢ ዕሁፉን አዳምጠው ይተረጉማሉ፡፡
- ➢ ለቃላዊ ግጥም ብያኔ ይሰጣሉ፡፡
- ➢ የቃላዊ ግጥም አይነቶችን ያብራራሉ፡፡
- ➢ የቅኔ ምንነት ይለያሉ፡፡
- ➢ ዜማውን ጠብቀው ግጥም ያነባሉ፡፡

## የትምህርት ይዘቶች

- አዳምጦ መተርጎም
- ግጥምን በቃል ማቅረብ
- ግጥም ማንበብ
- ቃላዊ ግጥም መፃፍ
- የቅኔ ምንነት
- ዘይቤያዊ አገላለፆችን መተርጎም
- አያያዥ ቃላት

## አንድ፡- ማዳመጥ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ማዳመጥ

**ተግባር**

- ✓ ተማሪዎች ምዕራፉን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን አጥጋቢ የመማር ውጤት አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚደግፉ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ በመገፋፋት ለትምህርቱ ያዘጋጇቸው፡፡
- ✓ በቅድመ ማዳመጥ ላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ስለቃላዊ ግጥም የማውቀው እና የማላውቀው የሚለውን ረድፍ ተማሪዎቹ በተናጥል እንዲሞሉት ያድርጉ፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ የምንባቡ ቅጂ አእንዲደርሳቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ የሰንጠረዡን መሙላታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ክፍተቱን ተመልክተው ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡

### የማዳመጥ ጊዜ

**ተግባር**

- ✓ ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ የኮከብ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ቆም በማለት የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ፡፡ በመቀጥልም የንባቡን ክፍል ይቀጥሉ፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ የምንባቡን ቅጅ ይስጧቸው፡፡

አድምጦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ተማሪዎቹ ወደ ሰንጠረዡ ተመልሰው ከምንባቡ ስለቃላዊ ግጥም ያወቅኩት የሚለውን ረድፍ እንዲሞሉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን መሰረት አድርገው የቀረቡት ጥያቄዎች የያዟቸው ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ሀሰት በማለት እንዲመልሱ ያድርጉ፤ እገዛም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ የቀረቡትን ቃላት ከተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡

"ቃላዊ ግጥም"

ስነ-ቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲወራረድ (ሲተላለፍ የመጣ) ቃላዊ ስነ-ጽሑፍ ነው፡፡ ስነ-ቃል በመነገር፣ በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ነው፡፡ የስነ-ቃል ዓይነቶች በርካታ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል ቃላዊ ግጥም አንዱ ነው፡፡

የሰው ልጆች ሀሳባቸውን በጽሑፍ መግለጽ ከመጀመራቸው በፊት ግጥምን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ግጥም ቃላዊ በሆነ መንገድ ሰፊ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ መልዕክትን በዜማና በቃል ስለሚያስተላልፍ ቃላዊ ግጥም እየተባለ ይጠራል፡፡

የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ እነሱም:- የአውዳመት፣ የፉከራ፣ የልመና፣ የሙሾ፣ የስራ ግጥሞች ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቃላዊ ግጥሞች እንደየሁኔታው ሊዜሙ ወይም በእንጉርጉሮ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ቃላዊ በመሆናቸው በአብዛኛው አጫጭር

ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላዊ ግጥሞች ምጣኔ፣ ምትና ዜማ አላቸው፡፡ ግጥሞቹ በአብዛኛው በእኩል ጊዜ እንዲያልቁ ሆነው የተመጠኑ ሀረጋትን ይይዛሉ፡፡ የተመጠኑት ሃረጋት በተወሰነ ጊዜ ሲደጋገሙ ደግሞ ምትን ይፈጥራሉ፤ ሲነበቡም ዜማ አላቸው፡፡ ግጥሙ እንደሚገልፀው ስሜት ዜማው ይለያያል፡፡

ቃላዊ ግጥም በግጥም መልክ ከሚቀርቡ ወይም ከሚዜሙ የስነ-ቃል ዓይነቶች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን በአብዛኛው የገጠሩ ህዝብ በጋራም ሆነ በተናጥል አንድ ስራ በሚያከናውንበት ጊዜ ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስራት ስለሚያግዘው ግጥም እየደረደረ ያንጎራጉራል፤ ይዘፍናል፤ይጨፍራል፡፡ ለምሳሌ ቡድናዊ የስራ አጋጣሚዎች ላይ ለምሳሌ፡- ቤት ሲሰራ፣ አጥር ሲያጥር፣ እርሻ ሲያርስ፣ ሲያርም፣ ሲያጭድና ሲወቃ ወዘተ. ልዩ ልዩ ስራዎችን ሲያከናውን ያዜማል፡፡ በተናጥል ቢሆንም ማንጎራጎር የተለመደ

ነው፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከቀረበው ምንባብ ምን ተረዳችሁ? ቀጥሎ የቀረበው ቃላዊ ግጥም ሰዎች ምን ሲሰሩ የሚዜም ይመስላችኋል? መልእክቱስ ምንድነው ?

ሄደ ነጎደ ሄደ ወረደ፣

ማጭዱ እንደሳት እየነደደ፣

የቆመውን ጤፍ እየጎመደ፡፡

ቃላዊ ግጥሞች ደራሲያቸው አይታወቅም፤ የኔ ባይ ባለቤት ስለሌላቸው የህዝብ ሃብት ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ከሁኔታዎች ጋር ለማስማማት ሲባል በየጊዜው ማሻሻያዎችና ለውጦች ይደረግባቸዋል፤ የበርካታ ሰዎች አሻራም ያርፍባቸዋል፡፡ ቃላዊ ግጥሞች በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡

በቃል እየተላለፉ ረዥም እድሜ ያስቆጠሩ በመሆናቸው የሰው ልጆችን ታሪክ ማጥናት ሲፈለግ እንደመረጃ ምንጭ ያገለግላሉ፤ የቋንቋ አጠቃቀማቸው የተመረጠና ቁጥብ ስለሆነ ሲዜሙ አድማጭን ያዝናናሉ፤ ያመራምራሉ፤ እርካታም ይፈጥራሉ፤ ከሁኔታዎች ጋር አስማምቶ መጠቀምን ስለሚፈቅዱ የፈጠራ ችሎታን ያጎለብታሉ፤ የተለያዩ ጉዳዮችን በተመለከተ በርካታ ቁም ነገሮች ስለያዙ አስተማሪነታቸው ከፍተኛ ነው፤ መልካም ስነ-ምግባሮች ተጠብቀው እንዲዘልቁ ለማድረግ ያስችላሉ፤ ለዘመናዊ ገጣሚዎችም ቢሆን መነሻ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ይህም በመሆኑ በብዙ ዘመናዊ ግጥሞች ውስጥ ቃላዊ ግጥሞችን በአይነትና በብዛት ማግኘት የተለመደ ነው፡፡

የአንድ ማህበረሰብ ባህል በቃላዊ ግጥሞች አማካኝነት ጎልቶ ይወጣል፡፡ የማህበረሰቡ የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ ወዘተ. ልማድ በግጥሞቹ ይተላለፋል፡፡ ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸው አመለካከት ፤ እምነትና ፍልስፍና ሁሉ በቃላዊ ግጥሞች ይንፀባረቃል፡፡ ስለሆነም እንደሌሎች ቅርሶች ሁሉ እነዚህን ጠቃሚ ሃብቶቻችንን ልንጠብቃቸው ይገባል፡፡

(አንተነህ፣ 2001፣ የአማርኛ ስነ- ቃል አጭር ቅኝት እና ዘሪሁን፡፡1992፡፡የስነ- ፅሁፍ መሰረታዊያን፡፡ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ) ፡፡

ምዘና፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- ስለቃላዊ ግጥም ምንነትና አይነቶች ጥያቄ ይጠይቋቸው

መርጃ መሳሪያ፡-

- መቅረፀ ድምፅ (አስፈላጊ ከሆነ)
- የቃላዊ ግጥም አይነቶችን የሚያሳይ ምስል

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ፡-

ከታች የቀረቡት ከማዳመጥ ምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ሀሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. እውነት

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ሸ | 5. ሀ |
| 2. ሐ | 6. በ |
| 3. ሠ | 7. ለ |
| 4. ረ | 8. መ |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### የትምህርቱ አቀራረብ

**ማስታወሻ**

**የግጥም ሙያዊ ቃላት**

ስለ ግጥም ስናወራ ስለግጥም ሙያዊ ቃላት ማንሳታችን አይቀርም፡፡ የግጥም ሙያዊ ቃላት የሚባሉት ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ናቸው፡፡

1. ስንኝ ፡- በግጥም ውስጥ ተጽፎ የሚገኝ የግጥም አንድ መስመር ነው፡፡
2. ሀረግ፡- በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ የስንኝ ክፍል ነው፡፤
3. ቤት፡- በግጥም ውስጥ በየስንኙ መጨረሻ ላይ የሚገኝ ፊደል ነው፡፡
4. አንጓ (አርኬ)፡- በግጥም ውስጥ አንድ ሀሳብ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የስንኞች ስብስብ ነው፡፡
5. ቤት መምቻ፡- በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ ስንኞች ውስጥ የመጀመሪያው ስንኝ የመጨረሻ ቃል ቤት መምቻ ይባላል፡፡
6. ቤት መድፊያ፡- በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ ስንኞች ውስጥ የመጨረሻው ስንኝ የመጨረሻ ቃል ቤት መምቻ ይባላል፡፡

ተግባር አንድ

- ✓ ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎች ይስጧቸው፣ ገለጻም ያድርጉላቸው፡፡

- ✓ ተማሪዎች ራሳቸው ወይም ሌሎች ሰዎች የሚያዜሟቸውን ቃላዊ ግጥሞች ሰብስበው እንዲመጡ ያድርጉ።

ተግባት ሁለት

- ✓ ተማሪዎቹ ሰብስበው ያመጡትን ቃላዊ ግጥሞች በክፍል ውስጥ እንዲከውኑ ያድርጉ፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው።

ምዘና፡-

- የሚያውቋቸውን ቃላዊ ግጥሞች መናገራቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የግጥም ሙያዊ ቃላትን ለማስረዳት የሚያገለግል ናሙና ግጥም

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ

ቅድመ ማንበብ

ተግባር

- ✓ ተማሪዎች ወደ ማንበብ ሂደት ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ የተማሪዎችንም ምላሽ ይቀበሏቸው።

- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ጥያቄዎቹን በቃል ያብራሩላቸው፤ ስዕሉን በተመለከተ ገለፃ ያድርጉላቸው።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

- ✓ ወደ ምንባቡ በማለፍ እስከ ንባብ ጊዜ ጥያቄ ያሉትን አንቀፆች ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በእርሶ መሪነት ተማሪዎችን ካሰሯቸው በኋላ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲያነቡ ያድርጉ፤ ይከታተሏቸው፡፡
- ✓ የመስማት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ ንባቡን ራሳቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፤ የንባቡን ቅጂ ይስጧቸው፤ ድጋፍም ይስጧቸው፡፡

አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ

- ✓ ተማሪዎቹ ንባባቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመሄድ ተግባር አንድ ላይ ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በጽሑፍ አጭር መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት

- ✓ የቀረቡትን የቃላዊ ግጥሞች አይነት በቀረበው ምሳሌ መሰረት እንዲለዩ ያድርጉ፤ እገዛም ይስጧቸው፡፡

ተግባር ሶስት

- ✓ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ በቡድን እንዲወያዩ

ያድርጉ፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡

ተግባር አራት

ከማስታወሻው በታች የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞችና ቅኔን ዜማቸውን ጠብቀው እንዲያነቡ ያድርጉ፤ በስርዓት ማንበባቸውንም ይከታተሉ፡፡

ምዘና፡-

- የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች አይነት መለየታቸውን ያረጋግጡ
- የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞችና ቅኔን ዜማቸውን ጠብቀው ማንበባቸውን ያረጋግጡ

መርጃ መሳሪያ፡-

- የቃላዊ ግጥም አይነቶችን የሚያሳይ ምስል

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት

ከታች የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች አይነት ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

1. የሀዘን
2. የሰርግ
3. የስራ
4. የቀረርቶ
5. ፉከራ
6. የልመና
7. የልጆች ጨዋታ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

✓ የቀረቡትን ያልተሟሉ ቃላዊ ግጥሞች አሟልተው እንዲጽፉ ያድርጉ፤ እገዛም ያድርጉላቸው፡፡

ተግባር ሁለት

✓ በተማሩት መሰረት ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥሞችን ጽፈው በመምጣት በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጉ፤ ድጋፍም ይስጧቸው፡፡

ምዘና፡-

- የቀረቡትን ያልተሟሉ ቃላዊ ግጥሞች አሟልተው መጻፋቸውን ያረጋግጡ
- በተማሩት መሰረት ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥሞችን መጻፋቸውን ይመልከቱ

መርጃ መሳሪያ፡-

- ቃላዊ ግጥሞችን የያዘ ቻርት

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

ከታች የቀረቡትን ያልተሟሉ ቃላዊ ግጥሞች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

1. አንድ ሰው ሞተ
2. አስተማረው
3. እድሌ ነውና
4. አስመሰለችው
5. ከመንገድ ቆረጠው
6. እሱን ሳነክት

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር

- ✓ ስለዘይቤ የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎች ይስጧቸው፤ ገለፃም ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ የሰጧቸውን ማስታወሻና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡

**ማስታወሻ፤ ዘይቤ**

ዘይቤ (ዘይቤያዊ ንግግር)፦የምናስተላልፈው መልዕክት ምስል በመፍጠር መልዕክቱ ጎልቶ፣ አምሮና ደምቆ እንዲታይ የምንጠቀምበት የአነጋገር ስልት ነው፡፡

የዘይቤ አይነቶች፡- በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በጣም በርካታ የዘይቤ አይነቶች ቢኖሩም የተለመዱት እና ዘወትር የምንጠቀምባቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሰውኛ ዘይቤ፡- የሰውን ልዩ ልዩ ባህሪያት፣ ድርጊት እና ችሎታ ሰው ላልሆኑ ነገሮች ለምሳሌ፡- ለእንስሳት፣ ለተክሎች፣ ለግዑዛን ነገሮች ወዘተ. በመስጠት የሰውን ተግባር ሲፈፅሙ የሚያሳይ የዘይቤ አይነት ነው፡፡

   ምሳሌ፡- "ለሰው ሞት አነሰው" አለች ቀበሮ

2. አነፃፃሪ ዘይቤ፡- ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀሳቦችን፣ ባህሪዎችን፣ ድርጊቶችን ወዘተ. በማነፃፀር የሚያቀርብ የዘይቤ አይነት ነው፡፡ ሲያነፃፅርም እንደ፣ ያህል፣ ይመስል፣ ልክ ወዘተ. የሚሉ ቃላትን ይጠቀማል፡፡

   ምሳሌ፡- እንደ ደራሽ ውሃ ድንገት ከተፍ አለች፡፡

3. ተለዋጭ ዘይቤ፡- የአንድን ነገር ባህሪ ሙሉ በሙሉ ለሌላው በመስጠት የሚቀርብ የዘይቤ አይነት ነው፡፡ ይህ የዘይቤ አይነት ነው፣ ናቸው፣ ሆነ ወዘተ. የሚሉ ቃላትን ይጠቀማል፡፡

   ምሳሌ፡- ንግግሯ እሬት ነው፡፡

4. አያዎ ዘይቤ፡- አይ+አዎ = አያዎ   አያዎ ዘይቤ ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦችን አንድ ላይ አጣምሮ የሚያቀርብ ላይ ላዩን ሲያዩት እውነት የማይመስል ሲመረምሩት ግን እውነትነት ያለው የዘይቤ አይነት ነው፡፡

   ምሳሌ፡- እሱ የልጅ አዋቂ ነው፡፡

5. <u>እንቶኔ ዘይቤ</u>፦ በአጠገብ የሌለን አካል በቅርባችን እንዳለ፣ እንደሚሰማ እና መልስ እንደሚሰጥ በመቁጠር በመጠየቅ፣ በመውቀስ፣ በማውራት ወዘተ. የሚቀርብ የዘይቤ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፦ ተናገር አንተ ሀውልት አክሱም ላይ ያለኸው፣

እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ ጉድ ያየኸው፡፡

6. <u>ተምሳሌት ዘይቤ</u>፦ የተምሳሌት ዘይቤ ዋንኛ ባህሪ ውክልና ነው፡፡ አንድ ተጨባጭ ነገር ለሌላ ነገር በመቆም ያንን የሚወክለውን ነገር አጉልቶ የሚያሳይ የዘይቤ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፦ ርግብ የሰላም ተምሳሌት ነው

7. <u>ግነት ዘይቤ</u>፦ ትንሽ እውነታን በመያዝ ከነባራዊው እውነታ ጨምሮና አጋኖ የሚያቀርብ የዘይቤ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፦ የቤታችን ሳሎን ፈረስ ያስጋልባል!

8. <u>ምፀት ዘይቤ</u>፦ አንድን ሀሳብ በተቃራኒው የምንገልፅበት የዘይቤ አይነት ነው፡፡ የሚያሞግስ መስሎ የሚሳደብ፤ ያከበረ መስሎ የሚያዋርድ የጎንዮሽ አገላለፅ ነው፡፡

ምሳሌ፦ እሰይ የኔ ጀግና¡ የቤቱን እቃ ጨረስከው አይደል?

ምዘና፦

- ለቀረቡት የዘይቤዎች አይነቶች መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፦

- የዘይቤ አይነቶችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር፦

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ማስታወሻና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ።

1. ለ
2. ሀ
3. ሀ
4. ሐ
5. ሐ
6. መ
7. መ

## ክፍል ስድስት፦ ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

ተግባር አንድ

- ✓ በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ።

ተግባር ሁለት

- ✓ እስካሁን ስለውስብስብ ዓረፍተ ነገር በተማሩት መሰረት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አምስት ውስብስብ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፤ እገዛም ይስጧቸው።

ምዘና፦

- አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መመስረታቸውን ይመልከቱ

መርጃ መሳሪያ፦

- የአያያዥ ቃላትን ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

ቀጥለው በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. እንደ
2. ቢሆንም
3. ስለ
4. ይሁን እንጂ
5. በ
6. በተጨማሪ

## ዋቢ ፅሁፎች

መስፍን ሀብተማሪያም፡፡ 1983 ፡፡ አውደ ዓመት ፡፡ አዲስ አበባ ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ማርታ እሸቱ ፡፡ 2007 ፡፡ ኩራዝ አማርኛ ፡፡ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ ኢንተርሽናል አሳታሚ ድርጅት፡፡

ሪፖርተር ጋዜጣ፤ ጥር 18 ቀን፤ ቅፅ 19 ቁጥር 1434፤2006 ዓ.ም፡፡

ሪፖርተር ጋዜጣ፤ መስከረም 18 ቀን ፤ቅጽ 25 ቁጥር 2026፤2012 ዓ.ም፡፡

ሰለሞን ሐለፎም ፡፡1997፡፡ የድርሰት አፃፃፍ፡፡ አዲስ አበባ፤ ብራና ማተሚያ ቤት፡፡

ሰለሞን ጥላሁን እና ስምረት ገብረ ማሪያም፡፡ 2000፡፡ ደማቆቹ የአንዳንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊያን የሕይወት ውልብታ፤አዲስ አበባ፡፡(ህትመት ፐፕሊኬሽን ሚዲያ ሴንተር ኢትዮጵያ)

ባየ ይማም፡፡ 2002፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች፡፡

ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወልደ መስቀል 2007 ፡፡ ስብስብ ስራዎች፡፡ አዲስ አበባ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡ (ሁለተኛ እትም)

ተምሳሌት እፁብ ድንቅ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች፤ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት፡፡ 2007፡፡ አዲስ አበባ፤ ፀሀይ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት፡፡

ታለጌታ ይመር ፡፡ 2007 ፡፡ ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ አጋዥ መፅሀፍ ከ7ኛ-10ኛ ክፍል ፡፡ አዲስ አበባ፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

አለም እሸቱ፡፡ 1999፡፡ ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ ከ7ኛ- 10ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፤ ብራና ማተሚያ ቤት፡፡

አለም ፀሀይ ወዳጆ ፡፡ 2009 ፡፡የማታ እንጀራ የግጥም መድብል ፡፡ አዲስ አበባ፤ ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

አብዱ ራህመቶና ንጉሴ አየለ ::1979:: ሙሽራው :: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ሐምሌ 25/2013 ዓ.ም::

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ቁጥር 285፣ሰኔ 15/2011 ዓ.ም::

ኢካሽ 25ኛ ዙር የጋዜጠኝነት ሰልጣኞች መጽሄት:: የካቲት 2013 ዓ.ም፣ ኖቫ ማተሚያ ቤት::

ኤ.ሲ.ፒ. ኤሲ የትምህርት ቦርድ የት/ቤት የበጎ ፍቃደኞች መመሪያ ማኑዋል::

ከበደ ሚካኤል::1961:: ብርሃነ ህሊና :: አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት::

ወይ አዲስ አበባ መፅሄት፣ቅፅ 1፣ቁጥር8፣2013ዓ.ም::

ዘሪሁን አስፋው:: 1992:: የሥነጽሑፍ መሠረታውያን:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::

ዝክረ ህዳሴ አዲስ አበባ መጽሄት፣2013 ዓ.ም::

የሻው ተሰማ ::1996:: ልሳነ-ብዕር ከመልሳነ ሰብእ :: አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት የታተመ::

የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር:: የ2006 ዓ.ም በጀት ዓመት ሪፖርት::

ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ ::1999:: አማርኛ አጋዥ መጽሀፍ :: አዲስ አበባ፣አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት

ጂ አይ ዜድ (GIZ) የጀርመን የተራዶ ድርጅት፣ 2020 እ.ኤ.አ የታተመ::

ጌታሁን አማረ:: 2008:: ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ :: አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች::

ጠና ደዎ:: 2008:: ሰው፣ ግብረገብና ስነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት

# የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 |
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | |

**አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ሰባተኛ ክፍል አንደኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት**

**ምዕራፍ አንድ፡-ተፈጥሮን ማድነቅ (18) ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ የትምህርት ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የሌሎችን ሀሳብ ያዳምጣሉ፡፡
- ስለተፈጥሮ ምንነት ይወያያሉ፡፡
- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ጽሁፍ ያነባሉ፡፡
- የተፈጥሮን የተለያየ ገጽታ ያደንቃሉ፡፡
- አንቀጽ ይመሰርታሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃመሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ የሌሎችን ሃሳብ በአትኩሮት ያዳምጣሉ፡፡<br>➢ የቋንቋውን አውድ ጠብቀው በቋንቋው ይጠቀማሉ፡<br>➢ ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መጽሃፍ በትክክል ያነባሉ፡፡<br>➢ ተለምዶአዊ ሃሳቦችን ተጠቅመው አንቀጽ | ማዳመጥ<br>መናገር<br>ማንበብ<br>መጻፍ<br>ቃላት<br>ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-ተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ጥያቄ በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>**ለምሳሌ፡- ስለወንዝ አጠቃቀም ምን ታውቃለችሁ፡፡**<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**መምህሩየሚያነብላቸውን አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ የአባይ ወንዝ<br>**ድህረ ማዳመጥ** ከተነበበው ጽሁፍ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br>**ተገቢ** የቋንቋ አጠቃቀም ተጠቅመው ተፈጥሮን እንዲያደንቁ ማድረግ፡፡በተሰጣቸው ርዕስ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>**ቅድመ ንባብ** የቀደመ እውቀታቸውን መሰረት ያደረጉጥያቄዎችበመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ | ➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>○ ለምሳሌ አባይ የት ይገኛል<br>➢ ስለተፈጥሮ መጠየቅ<br>○ ለምሳሌ አስኪ የአባይን ጥቅም ግለጹ<br>➢ የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላትን ለይተው እንዲወያዩባቸው ማድረግ<br>➢ የአንቀጹን ሃይለቃል እንዲያወጡ ማድረግ<br>➢ ለተለመዱ ቃላት ብያኔ እንዲሰጡ ማድረግ<br>➢ ስለቋንቋው መሰረታዊ መወቅር መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃመሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ይመሰርታሉ፡፡<br>➢ ለተለመዷዊ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡<br>➢ የመጀመሪያ ቋንቋን መሰረታዊ መዋቅር ይለያሉ፡፡ | | ለምሳሌ ስለተፈጥሮ ምንታውቃላችሁ<br>**በለሆሳስያ** ንባብ በትክክል እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ጥያቄ መጠየቅ<br>**ድህረ ንባብ** ምንባቡን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ሰእል ሊያስፈልግ ይችላል፡፡የቀረበላቸውን ስእል መሰረትአድርገውአንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡<br>ለተለምዷዊ ቃላት ብያኔ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡<br>መሰረታዊ የቋንቋ መዋቅርን በተመለከተ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ | |

**ምዕራፍ ሁለት የቤተሰብ እቅድ (9 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቅውጤት**

**ከዚህ የምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- ➢ በጥሞና ያዳምጣሉ፡፡
- ➢ በቤተሰብ እቅድ ምንነት ላይ ይወያያሉ፡፡
- ➢ ቀላል ሁነቶችን ይተርካሉ፡፡
- ➢ የቤተሰብ እቅድን መሰረት አድርገው በሚሰጡ አስተያየቶች ላይ ይከራከራሉ፡፡
- ➢ ስዕሎችን ያነባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-<br>• ጽሁፉን በአትኩሮት ያዳምጣሉ፡፡<br>• ቀላል ሁነቶችን በቅደም ተከተል ይተርካሉ፡፡<br>• አንብበው ስእሎችን ይገልጻሉ፡፡<br>• በ ሶስት አንቀጽ ኢመደበኛ ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡<br>• አዳዲስ ቃላትን ለይተው ትርጉም ይሰጣሉ፡፡<br>• የንቋውን መሰረታዊ መወቅር ጠብቀው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡ | • ማዳመጥ<br>• መናገር<br>• ማንበብ<br>• መጻፍ<br>• ቃላት<br>• ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-የኂላ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>ምሳሌ ስለቤተሰብ ምን ታውቃላችሁ<br>**በማዳመጥ ጊዜ** ፡-እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ፡፡<br>ምሳሌ ቤተሰብ<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ካዳመጡት ውስጥ የወጡ ጥቄዎችን መጠየቅ<br>ቀላል ሁነቶችን በቅደም ተከተል እንዲተርኩ ማድረግ<br>ስለ ቤተሰብ አቅድ እንዲወያዩ ማድረግ<br>ስለርአሱ የተለየዩ ጥያቄዎች መጠየቅ<br>ቅድመ ንባብ የቀደመ እውቀትን በመጠየቅ ማነቃቃት<br>ምሳሌ ስለቤተሰብ አቅድ ምን ታውቃለችሁ<br>የንባብ ጊዜ ስዕሉን አይተው እንዲገልጹ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ<br>ድህረ ንባብ ምንባቡን መሰረት አድርገው ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ( ስዕል ያስፈልጋል )<br>መረጃ ሰብስበው ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>በሶስት አንቀጽ አስረጅ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>ጽሁፋቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተራረሙ | • ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>ምሳሌ፡, የቤተሰብ እቅድ ምን ማለት ነው<br>• የቤተሰብ አቅድን አሰፈላጊነት መጠየቅ<br>• የምንባቡን ዋና ሃሳብ እንዲያጠቃልሉ መጠየቅ<br>• የያንዳንዱን አንቀጽ ሀይለቃል አንዲያወጡ መጠየቅ<br>• የተወሰኑ አዳዲስ ቃላትን አንዲገልጹ መጠየቅ<br>• የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅር አንዲገልጹ መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | ማድረግ<br>ከቀረበላቸው ጽሁፍ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ<br>ቋንቋን መሰረታዊ መዋቅር ጠብቀው ዓ. ነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ | |

**ምዕራፍ 3 በጎፍቃደኝነት (9 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ የትምህርት ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- ያደመጡትን ያንጸባርቃሉ፡፡
- ስለበጎ ፍቃደኝነት ይገልጻሉ፡፡
- የጽሁፉን ዋና ሀሳብ መልሰው ይገልጻሉ ፡፡
- በጎ ፍቃደኞች በምን በምን ዙሪያ እንደተሰማሩ ይለያሉ ፡፡
- ከጽሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ያወጣሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህረት በኋላ :-<br>➢ ያደመጡትን መልሰው ያንጸባርቃሉ ::<br>➢ ከጓደኞቻቸው ጋር ምልልስ ያካሂዳሉ ::<br>➢ አንብበው የጽሁፉን ዋና መልዕክት እንደገና ይገልጻሉ::<br>➢ ካነበቡት ውስጥ ተዘውታሪ ቃላት ያወጣሉ::<br>➢ አራት አንቀጽ ያለው ቀስቃሽ ጽሁፍ ይጽፋሉ ::<br>➢ ለድርብ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ ::<br>➢ የቃላትን ነጠላ እና ብዙ ቁጥር ቅርጽ ይለያሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-የኋላ** እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት::<br>ምሳሌ በጎፍቃደኝነት ምንድነው<br>**በማዳመጥ ጊዜ** አጫጭር ንግግር በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ እና ሌሎች አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ<br>ምሳሌ መረዳዳት<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የሚሰሯቸው ስራዎች መስጠት<br>ስለመረዳዳት እንዲገልጹ ማድረግ<br>ስለ መረዳዳት አጭር ምልልስ እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>**ቅድመ ንባብ** ቁልፍ ቃላትን ከምንባቡ እንዲያወጡ ማደርግ<br>ምሳሌ በጎፍቃደኝነት<br>**የንባብ ጊዜ** ምንባቡን አንብበው ዋናውን ሀሳብ እንደገና እንዲገልጹ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ<br>**ድህረ ንባብ** ምንባቡን መሰርት አድርገው ጽሁፋዊ ስራዎችን እንዲጽፉ ማድረግ<br>( የቃላት ሰንጠረዥ ያስፈልጋል ) | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ ምሳሌ የመረዳዳት አስፈላጊነት ምንድነው<br>➢ እርስ በእርስ መረዳዳት ያለውን ጥቅም እንዲገልጹ ማድረግ<br>➢ የምንባቡን ዋና ሃሳብ እንዲያጠቃልሉ ማድረግ<br>➢ በምንባብ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ<br>➢ ከአንቀጽ ውስጥ ሀይለ ቃል እንዲያወጡ ማድረግ<br>➢ ለድርብ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ<br>➢ ስለብዙ እና ነጠላ ቁጥር ቅርጾች መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | በሶስት አንቀጽ አሳማኝ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ( በጎ ፍቃደኝነት )<br>ጽሁፋቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተራረሙ ማድረግ<br>ለድርብ ቃላት ብያኔ እንዲሰጡ ማድረግ<br>የነጠላ እና ብዙ ቁጥር ቅርጾችን እንዲለዩ ማድረግ | |

**ምዕራፍ አራት የታዋቂ ሰዎች የህይወት ታሪክ (12 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቅውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- በማዳመጥ ያብራራሉ ፡፡
- የህይወት ታሪክን ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- ከጽሁፉ ውስጥ የምክንያት እና የውጤት ግንኙነትን ይለያሉ ፡፡
- የታዋቂ ሰው የህይወት ታሪክ ይጽፋሉ ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-<br>➢ አዳምጠው የጽሁፉን ሀሳብ ያደንቃሉ ።<br>➢ መመሪያዎቹን በተመለከተ በቡድን ይወያያሉ ።<br>➢ ተዘውታሪ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ይገልጻሉ ።<br>➢ አያያዥ ቃላትን ይለያሉ<br>➢ የተለመዱ ቃላትን ለተለያዩ አላማ ይጠቀማሉ ።<br>➢ ሀረግን ይገልጻሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-የኂላ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>ምሳሌ ስለ ህይወት ታሪክ ምን ታውቃላችሁ<br>**በማዳመጥ ጊዜ** አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ፡፡<br>ምሳሌ ታወቂ ሰው<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ያዳመጡትን መሰረት አድርው የሚሰሯቸው ጥያቄዎች መስጠት<br>የህይወት ታሪክ አጻጻፍን እንዲለማመዱ ማድረግ<br>መመሪያዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>ለህይወት ታሪክ እንዲለማመዱ ማድረግ<br>**ቅድመ ንባብ** ስለፈሊጣዊ አነጋገሮች መጠየቅ<br>ምሳሌ ከፈረሱ ጋሪው<br>**የንባብ ጊዜ** ምንባቡን አንብበው ዋናውን ሀሳብ እንደገና አንዲገልጹ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ<br>**ድህረ ንባብ** ምንባቡን መሰርት አድርገው ጽሁፋዊ ስራዎችን እንዲጽፉ ማድረግ<br>የተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እንዲናገሩ ማድረግ ( የህይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያ ያስፈልጋል ) | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ ምሳሌ የህይወት ታሪክ ስንጽፍ የምንከተላቸው ቅደም ተከተላዊ መንገዶች ምንድናቸው<br>➢ ስለአንድ ታዋቂ ሰው የህይወት ታሪክ እንዲናገሩ ማድረግ<br>➢ የምንባቡን ዋና ሃሳብ እንዲያጠቃልሉ ማድረግ<br>➢ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ የምንከተላቸውን ቅደም ተከተሎች እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ስማዊ ሀረግ እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ የተለመዱ ቃላትን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲያንጸባርቁ ማድረግ<br>➢ ስለስማዊ ሀረግ መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | መሸጋገሪያ ቃላትን እንዲጽፉ ማድረግ<br>በመሸጋገሪያ ቃላት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>ሀሳባቸውን ለመግልጽ የተለመዱ ቃላትን እንዲጠቀሙ ማድረግ<br>ከዓ.ነሮች ውስጥ ሀረጎችን እንዲለዩ ማድረግ | |

**ምዕራፍ አምስት ውሃናጥቅሙ (9 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- ከሚደመጡ ንግግሮች ውስጥ ማስታወሻ ይይዛሉ ፡፡
- ስለውሃ ጥቅም ይገልጻሉ፡፡
- የራሳቸውን ዝንባሌ እና ፍላጎት ይገልጻሉ ፡፡
- በርካታ ቃላትን ይዘረዝራሉ ፡፡
- የውሃ አይነቶችን ይዘረዝራሉ ፡፡

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-<br>➢ የጽሁፉን ይዘት ይገነዘባሉ<br>➢ ቀላል መረጃዎችን ይጠይቃሉ<br>➢ የምክንያት እና ወጤት | ማዳመጥ<br>መናገር<br>ማንበብ<br>መጻፍ<br>ቃላት<br>ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-የኋላ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>ምሳሌ የውሃ ጥቅም ምንድነው<br>**በማዳመጥ ጊዜ** አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ፡፡<br>ምሳሌ ውሃን በአግባቡ መጠቀም | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>○ ምሳሌ የውሃ አይነቶችን ዘርዝሩ<br>➢ ውሀን እንዴት በአግባቡ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ግንኙነትን ይለያሉ ፡፡<br>➢ ጽሁፍ ይተርካሉ ፡፡<br>➢ የቃላትን ፍካሪያዊ ፍቺ በመለየት ትርጉም ይሰጣሉ<br>➢ ገቢርና ተገቢሮዓ. ነገርን ይዘረዝራሉ ፡፡ | | **ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የሚሰሯቸው ስራዎች መስጠት<br>ሰለ ውሃ አይነቶች መረጃ ሰብስበው እንዲወያዩ ማድረግ ( የሚጠጣ እና የማይጠጣ )<br>**ቅድመ ንባብ** ስለምክንያት እና ውጤት ግንኙነት መጠየቅ<br>**የንባብ ጊዜ** ምንባቡን አንብበው የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት እንዲለዩ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ<br>ድህረ ንባብ ምንባቡን መሰርት አድርገው ምክንያት እና ውጤትን የተመለከቱ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ<br>በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ተራኪ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>ከጓደኞቻቸው ጋር ጽሁፍ እንዲያስተካክሉ ማድረግ<br>የቃላትን እማሬያዊ ፍቺ በተመለከተ እንዲያብራሩ ማድረግ<br>ገቢርና ተገቢሮ ዓ. ነገሮችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ | መጠቀም እንዳለባቸው መረጃዎችን እንዲሰበስቡ ማድረግ<br>➢ ከምንባቡ ውስጥ የውሃ አያያዝ ዘዴን እንዲገልጹ ማድረግ<br>➢ አንድ ተራኪ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ<br>➢ ለተወሰኑ ቃላት እማሬያዊ ፍቺዎቻቸውን አንዲገለጹ ማድረግ<br>➢ የተለመዱ ቃላትን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ገቢርና ተገቢሮ ዓ. ነገሮችን ልዩት እንዲገልጹ ማድረግ |

አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ሰባተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

## ምዕራፍ ስድስት፡- የሰዎች ዝውውር (9 ክፍለጊዜ)

### የሚጠበቀው ውጤት

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- ካዳመጡት ነገር በመነሳት ዋናውን ሀሳብ ይገልጻሉ፡፡
- የሰዎችን ዝውውር ጽንሰሃሳብ ይገልጻሉ፡፡
- ከጓደኞቻቸው ጋር በራስ በመተማመን ይናገራሉ፡፡
- በትክክል ያነባሉ፡፡
- የሰዎች ዝውውር የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ይገልጻሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-<br>➢ ያዳመጡትን ተገንዝበው ይተነትናሉ ፡፡<br>➢ በራስ በመተማመን ይናገራሉ<br>➢ የተሰጠውን ጽሁፍ በትክክል ያነባሉ ፡፡<br>➢ የገላጭ ጽሁፍን መዋቅር ያብራራሉ<br>➢ የቃላትን እማሪያዊ ፍቺ ይገልጻሉ<br>➢ የዓ.ነገር አይነቶችን ከአገልግሎታቸው አንጻር | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-የኋላ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>ምሳሌ የሰዎች ዝውውር ምንድነው<br>**በማዳመጥ ጊዜ** አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ፡፡<br>ምሳሌ የሰዎች ዝውውር ስጋት<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ያዳመጡትን መሰረት አድርው የሚሰሯቸው ስራዎች መስጠት<br>ሰለ ሰዎች ዝውውር ጠንካራ እና ደካማ ጎን እንዲወያዩ ማድረግ<br>ቅድመ ንባብ ስለርዕሱ መጠየቅ (ሰለ ሰዎች ዝውውር ምንታውቃላችሁ )<br>የንባብ ጊዜ ምንባቡን በትክክል እንዲያነቡ | • ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>ምሳሌ የሰዎች ዝውውር የሚያደርሱት ተጽዕኖ ምንድናቸው<br>• ስለሰዎች ዝውውር ጉዳት መጠየቅ<br>• የምንባቡን የተለያዩ ክፍሎች መጠየቅ<br>• የሰዎች ዝውውርን የተመለከቱ ገላጭ ጽሁፎች እንዲጽፉ ማድርግ<br>• ለተወሰኑ ቃላት ፍካሪያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ<br>• ስለተተግባሪ ዓ. ነገሮች መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ይገልጻሉ | | ማድረግ (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ)<br>**ድህረ ንባብ** ትክክለኛ አነባበብ እንዲለማመዱ ማድረግ ( ስዕል ያስፈልጋል )<br>የገላጭ ጽሁፍን ቅርጽ ተገንዝበው እንዲወያዩ እና እንዲጽፉ ማድረግ<br>የቃላትን ፍካሪያዊ ፍቺ እንዲገልጹ ማድረግ<br>የዓ. ነገር አይነቶችን ከአገልግሎታቸው አንጻር እንዲለዩ ማድረግ | |

**ምዕራፍሰባት፡- ማህበራዊ ግንኙነት** (12 ክፍለጊዜ)

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- በጥልቀት ያዳምጣሉ ::
- የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፡፡
- በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ጽሁፍ ይጽፋሉ ::
- ድብልቅ ዓ.ነገር ይመሰርታሉ ::

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-<br>➢ መረጃ ሰጪ ጽሁፎችን በጥልቀት ያዳምጣሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-የቀደመ እውቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>ምሳሌ ማህበራዊ ግንኙነት ምንድነው<br>**በማዳመጥ ጊዜ** አጭር ምንባብ አዳምጠው | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>ምሳሌ የማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊነት ምንድነው<br>➢ የማህበራዊ ግንኙነትን |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| ➢ በተወሰኑ ርዕሶች ዙሪያ ከጓደኞቻቸው ጋር ይስማማሉ ፡፡<br>➢ የተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ይጠቀማሉ ፡፡<br>➢ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ጽሁፍ ይጽፋሉ<br>➢ የቃላትን ተመሳሳይ ያዛምዳሉ<br>➢ ተተግባሪ ዓ.ገርይመሰርታሉ | ➢ ሰዋሰው | ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ፡፡<br>ምሳሌ ማህበራዊነት<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ያዳመጡትን መሰረት አድርው የሚሰሯቸው ስራዎች መስጠት<br>በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲስማሙ ማድረግ<br>ምሳሌ የማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊነት<br>**ቅድመ ንባብ** ስለ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ጥቅም መጠየቅ<br>**የንባብ ጊዜ** በፈሊጣዊ አነጋገሮች ላይ ተመስርቶ የቀረበውን ጥያቄ እንዲያነቡ ማድረግ (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ)<br>**ድህረ ንባብ** ፈሊጣዊ አነጋገርን በተመለከተ ያነበቡትን ምንባብ ተገንዝበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ ( ስዕል ያስፈልጋል<br>በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት አካተው ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>የቃላትን ተመሳሳይ እንዲያዛምዱ ማድረግ<br>ተግባራዊ ዓ. ነገሮች እንዲመሰርቱ ማድረግ | አስፈላጊነት በተመለከተ ተወያይተው እንዲስማሙ ማድረግ<br>➢ የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት በተመለከተ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ተጠቅመው እንዲያጠቃልሉ ማድርግ<br>➢ ማህበራዊ ግንኙነትን የተመለከተ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ የቃላትን ተመሳሳይ እንዲያዛምዱ ማድረግ<br>➢ የተተግባሪ ዓ. ነገሮችን የተለያዩ ክፍሎች እንዲገልጹ ማድረግ |

**ምዕራፍ ስምንት፡- ሱስ (9 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- አዳምጠው ተመሳሳይ ጽሁፍ ይጽፋሉ ፡፡
- ሱስ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ይገልጻሉ ፡፡
- የጽሁፉን ዋና ሀሳብ በተመከተ ዘገባ ያቀርባሉ ፡፡
- አድማጨን መርዳት ይቻል ዘንድ ጽሁፍን እንደገና ይከልሳሉ ፡፡

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-<br>➢ ተመሳሳይ ጽሁፍ ይጽፋሉ<br>➢ ሀሳብ እንደገና ያዋቅራሉ<br>➢ የጹፉን ዋና መልዕክት በቃል ይናገራሉ ፡፡<br>➢ በጽሁፍ ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ<br>➢ የተለመዱ ቃላትንአውዳዊ ፍቺ ይገልጻሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-የቀደመ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>ምሳሌ ሱስ ምንድነው<br>**በማዳመጥ ጊዜ** አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ፡፡<br>ምሳሌ ሲጋራ ማጨስ<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ያዳመጡትን መሰረት አድርገው ተመሳሳይ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>ሀሳብን እንደገና በማዋቀር እንዲናገሩ ማድረግ ( የሲጋራ ማጨስ ተጽዕኖ)<br>(በመሃል ጥያቄ መጠየቅ)<br>ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው ጽሁፍ ባግባቡ እንዲጽፉ ማለማመድ ለተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ ውስብስብ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቂ መጠየቅ<br>ምሳሌ ሱስ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምንድነው<br>➢ ሀሳባቸውን እንደገና እንዲያዋቅሩ መጠየቅ<br>➢ ሱስ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በቃል እንዲያቀርቡ መጠየቅ<br>➢ ስርዐተ ነጥቦችን እንዴት እንደሚጠቀሙ መጠየቅ<br>➢ ለተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ መጠየቅ<br>➢ ድርብ ዓ. ነገሮችን እንዲያርሙ መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ውስብስብ የዓ. ነገር ይመሰርታሉ | | | |

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡-የአገር ፍቅር** (12 ክፍለጊዜ)

**የሚጠበቅውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- አዳምጠው የጽሁፉን ጽንሰሃሳብ ከህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ ።
- የሀገር ፍቅርን ምንነት ይገልጻሉ ።
- ለተወሰነ አላማ ያነባሉ ።
- የሀገር ፍቅርን ያደንቃሉ ።

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-<br>➢ ጽሁፉንአንብበው ከራሳቸው ህይወት ጋር ያዛምዳሉ<br>➢ በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ተወያይተው ከስምምነት ላይ ይደርሳሉ ።<br>➢ ለተወሰነ አላማ ያነባሉ ። | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-የቀደም እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት።<br>ምሳሌ የሀገር ፍቅር ምንድነው<br>**በማዳመጥ ጊዜ** አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ።<br>ምሳሌ የአደዋ ድል<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ያዳመጡትን መሰረት አድርው ከራሳቸው ጋር ማዛመድ | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>ምሳሌ የአር ፍቅር ውጤቱ ምንደነው<br>➢ ስለአገር ፍቅር ተወያይተው እንዲስማሙ ማድረግ ( የአድዋ ድል )<br>➢ ጽሁፉን በጥልቅ እንዲያነቡ ማድረግ<br>➢ ስለአገር ፍቅር ጽሁፍ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ የሥዕሉን መልዕክት በጽሁፍ ይገልጻሉ<br>➢ ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይገልጻሉ<br>➢ ውስብስብ ዓ. ነገር ይመሰርታሉ | | የአገር ፍቅርን አስፈላጊነት በተመለከተ ተወያይተው በሃሳቡ ላይ ከስምምነት እንዲደርሱ ማድረግ<br>**ቅድመ ንባብ** ስለ ርዐሱ መጠየቅ<br>ሰለአሀገር ፍቅር ምን ታውቃላችሁ<br>**የንባብ ጊዜ** ለተወሰኑ አላማዎች ምንባብ እንዲያነቡ ማድረግ (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ)<br>**ድህረ ንባብ** ምንቡን ተገንዝበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ ( ስዕል ያስፈልጋል )<br>አድዋን በተመለከተ የተሳሉ ስዕሎችን ጽሁፍ እንዲገልጹ ማድረግ<br>ከጓደኞቻቸው ጋር የተገለጸውን ጽሁፍ ማረም<br>ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት<br>የቋንቋውን ህግ ጠብቆ ውስብስብ ዓ.ነገር መመስረት | እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ<br>➢ ውስብስብ ዓ. ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ |

**ምዕራፍ አስር፡- ቃላዊግጥም (12 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- ጽሁፉን አዳምጠው ይተረጉማሉ ።
- ለቃል ስነ-ግጥም ብያኔ ይሰጣሉ ።
- የቃል ግጥም አይነቶችን ያብራራሉ ።
- የቅኔ ምንነትን ይለያሉ።
- ዜማውን ጠብቀው ግጥም ያነባሉ ።

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-<br>➢ ጽሁፉ አንብበው ይተረጉማሉ ።<br>➢ ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥም ይናገራሉ ።<br>➢ ዜማውን ጠብቀው ግጥም ያነባሉ ።<br>➢ ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥም ይጽፋሉ<br>➢ የቅኔ ምንነትን ይለያሉ<br>➢ ዘይቢያዊ ቃላትን | ማዳመጥ<br>መናገር<br>ማንበ<br>ብመጻፍ<br>ቃላት<br>ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-የቀደመ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት።<br>ምሳሌ ቃላዊ ግጥም ምንድነው<br>**በማዳመጥ ጊዜ** አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ።<br>ምሳሌ አጭር ግጥም<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ያካዳመጡትን መሰረት አድርው ከራሳቸው ጋር ማዛመድ<br>አዳምጠው ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥም እንዲናገሩ ማድረግ<br>**ቅድመ ንባብ** ስለርዕሱ መጠየቅ<br>ስለ ቃላዊ ግጥም ምን ታውቃላችሁ<br>**የንባብ ጊዜ** ተገቢውን አገላለጽ ተጠቅመው ምንባቡን | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቂ መጠየቅ<br>ምሳሌ የቃላዊ ግጥም መልዕክት ምንድነው<br>➢ ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥም እንዲናገሩ ማድረግ<br>➢ ቃላዊ ግጥም እንዲያነቡ ማድረግ<br>➢ ቃላዊ ግጥም እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ የቅኔ ምንነት እንዲሌ ማድረግ<br>➢ የዘይቤአዊ አባባሎችን |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ያብራራሉ<br>➢ በጽሁፍ ውስጥ አያያዦችን ይጠቀማሉ | | እንዲያነቡ ማድረግ (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ)<br>**ድህረ ንባብ** ምንባቡን ተገንዝበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ ( ተጨማሪ ቃላዊ ግጥም ያስፈልጋል )<br>ተመሳሳይ ቃላዊ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>ከጓደኞቻቸው ጋር የቃላዊ ግጥምንና ቅኔን ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱ ማድረግ<br>ዘይቤያዊ አገላላጾችን እንዲያብራሩ መጠየቅ | ትርጉም እንዲያብራሩ ማድረግ |

# አማርኛ

# እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## (፯) 7ኛ ክፍል